ጥር፣ 2000 ኢ.ም

# ያለፈውንና ያለንበትን አይቶ የወደፊቱን አቅዶ መንቀሳቀስ

## *አጭር መግቢያ*

ቅንጅት ዛሬ በገዛ አመራሩ በተለኮሰበት ቀውስ እየታመሰ ነው። ከእዚህ ውጭ በስልጣን ላይ ያለው መንግስትና የቅንጅትን መዳከም የሚፈልጉ ሃይሎች በህብረት ጥቃት ከፍተውበታል። ቅንጅትም አብዛኛውን ግዜውንና እና አቅሙን ለተፈጠረው ቀውስ መፍትሄ ፍለጋና የሚደርስበትን ጥቃት በመከላከል እያጠፋው ነው። በመሆኑም መሰረታዊ የሆኑ፣ ከድርጅታችን ህልውና፣ ከህዝብና ከሃገር እጣና ከተጀመረው የዴሞክራሲ ትግል ጋር የተያያዙ ግዙፍ ጥያቄዎችን ማንሳትና ምላሻቸውን በተገቢው መስጠት የሚችል አልሆነም።

የአንባቢን ትኩረት ለመሳብ የፈለግሁት ቅንጅት በማኒፌስቶው ግልጽ ባደረጋቸው የድርጅቱ ፖሊሲዎች ላይ አይደለም። ትኩረቴ ቅንጅት እነዚህን ፖሊሲዎቹን ለህዝብ ግልጽ አድርጎ፣ ለምርጫ ራሱን አዘጋጅቶ መንቀሳቀስ ከጀመረባቸው የ1997ቱ የቅድመ ምርጫ ወራት አንስቶ እስካለንበት ወቅት ድረስ በሃገራችን የሰፈነውን በቀውስ የተሞላ የፖለቲካ ሁኔታ የሚመለከት ነው። ባለንበት ወቅት መነሳት ያለባቸው ጥያቄዎች በርካታ ናቸው። ለምሳሌ ብቻ ጥቂቶቹን ልጥቀስ።

ከምርጫ 97 በፊት ቅንጅት በሃገሪቱ የፖለቲካ ሁኔታና በስልጣን ላይ ስላለው መንግስት የነበረው ግምገማ ምንድን ነበር? ይህ ግምገማ ከምርጫው በኋላና አሁን ከአለንበት ሲታይ ትክክል ነውን? ከምርጫና በኋላ በተለያዩ ወሳኝ ምእራፎች ቅንጅት የወሰዳቸው አቋሞች ምንድን ናቸው? ምንስ ያህል ትክክለኛ ነበሩ? ከምርጫ 97 በፊት፣ በምርጫው ወቅትና በኋላ የቅንጅት ድርጅታዊ ጥንካሬዎችና ድክመቶች ምንድን ናቸው? ከምርጫ 97 በኋላ በወያኔ የተካሄደው አስከፊ እመቃ በህብረተሰቡ የፖለቲካ ህይወት ላይ ያሳደረው ተጽእኖ ምንድን ነው? የምርጫ 97 አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች ምንድርን ናቸው? እነዚህ ገጽታዎች በሃገራችን ፖለቲካዊ መልክአ-ምድር ላይ ምን ተጨባጭ ተጽእኖዎች አሳድረዋል? በምርጫ 97 በሃገሪቱ የነበረው የሃይል አሰላለፍ ምን ይመስል ነበር? ዛሬስ ምን ይመስላል? ምርጫ 97 በስልጣን ላይ በሚገኘው የወያኔ አገዛዝ ላይ ምን አይነት ተጽእኖ አስከትሏል? ከሁሉ በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ በወያኔ የተወሰደው የግድያ፣ የእስራት፣ የማፈናቀል፣ ከሃገር የማሳደድ፣ የሰብአዊና የሲቪል መብቶች ግደባ፣ የፕሬስ ነጻነት ገፈፋና አፈና፣ ወታደሩን ፖሊሱን የጸጥታ ሃይሉን የበለጠ ዘረኛ በሆነ መንገድ አዋቅሮ በግልና በቡድን የተያዘን የስልጣንና የጥቅም ተከላካይነት ማስማራት፣ የዳኝነት ስርአቱን በካድሬ ዳኞች ሞልቶ በፍትህ መቀለድ፣ በጥቅሉ ይህ ዛሬ ያለምንም ማስመሰል የገዛ ህገመንግስቱን ሳይቀር በመጣስ በሀገራችን ላይ ምን ታደርጉኛላችሁ በሚል እብሪት የተንሰራፋው አገዛዝ ሰላማዊና ህጋዊ የፖለቲካ ትግል ዘይቤን በሚከተሉ ቅንጅትን በመሰሉ ድርጅቶች ላይ ምን ጫና እያሳደረ ነው? ወያኔ የፈጠረው አምባገነናዊ አፋኝ የፖለቲካ ሁኔታ ከወያኔ አሽከርነት ውጭ በነጻነት ለመንቀሳቀስ ለሚፈልጉ ሃይሎች የሃገራችንን የፖለቲካ መድረክ ክፍት ያደርጋል ወይ? አንድ አንድ እራሳቸውን ተቃዋሚ አድርገው የሚያዩ አካላትና የውጭ መንግስታት ወኪሎች እንደሚሉት "ልጅ የሰጡትን ይዞ ያለቅሳል በሚል ብሂል" ተመርተን የተጭበረበረውን ምርጫ ቅንጅት ተቀብሎ ፓርላማ በመግባት ጎደለኝ የሚላቸውን

ኢህአዴግ እንዲጨምርለት ማልቀስ ነበረበት ወይ? ለመሆኑ የወያኔ የፖለቲካ ርእዮተ-አለም፣ የድርጅቱ ባህርይና ጠባብ የህብረተሰብ መሰረቱን ግምት ውስጥ በመስገባት፣ በተለይ ደግሞ የህዝብን ስሜት በ1997 ምርጫ ወያኔ ካየ በኋላ፣ አንዳንዶቹ ተቃወሚዎች እንደሚሉት፣ በልመናና በመማጸንና፣ ሂሳዊ ድጋፍ በመስጠትና በማባበል በሃገራችንን ነጻና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ የሚደረግበትን ሁኔታ እንዲፈጥር ማበረታት ይቻል ነበር ወይ? በተለይ ህገ-መንግስቱን ማስከበር የሚችሉ አካላት በሌሉበት ሃገር በህገ-መንግስቱ የተደገገን ህጋዊ መብት በመጠቀም ብቻ በስልጣን ላይ ካላው የወያኔ አገዛዝ የሚሰነዘርን ቅጥ ያጣ በእብሪት የተሞላ ጥቃት መከላከያው ምንድነው? ሌላው መሰረታዊ ጥያቄ ዛሬ በሃገራችን ላይ የሰፈነውን የፖለቲካ ጨለማ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ ትግል መግፈፍ ይቻላል ወይ? የሚገፈፍበትስ አግባብ ምንድን ነው? ቅንጅትን የመሰለ የፖለቲካ ድርጅት ከላይ ባነሳኋቸው ጥያቄዎች ዙሪያ ግልጽነት ያለው መልስ እየሰጠ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

ከላይ ያነሳኋቸው ጥያቄዎች ከምሩ ለመመለስ የሚመክር የፖለቲካ ሰው የሃገራችን የፖለቲካ የገባበትን አሳሳቢ አጣብቂኝ በቀላሉ ለመገንዘብ የሚያዳግተው አይመስለኝም። እነዚህን ጥያቄዎች መመለስ የቅንጅት አመራር ሃላፊነት ቢሆንም፣ ቅንጅትን የሚደግፉ አቅሙ ያላቸው ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንም ከላይ የጠቀሱትን ጥያቄዎች በማንስትና ምላሻቸውንም በመስጠት ያቅማቸውን ማበርከት አለባቸው እላለሁ። የፖለቲካ እንቅስቃሲያችን ይህንን ማድረግ ካልቻለ በውቅያኖስ መሃል ኮምፓሱን እንደጠፋበት ጀልባ ይሆናል።

ይህን ጽሁፍ ለማዘጋጀትና በይፋ ለማሰራጨት ስነሳ አላማዬ ሁለት ነው። የመጀመሪያው፣ በበኩሌ አጣዳፊና ቅንጅት ወደፊት ለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች አስዋፅኦ ማድረግ ይችላሉ ብዬ ባመንኳቸው ጊዜያዊና መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የራሴን ሃሰብ በማቅረብ ትግሉን ለመደገፍ ነው። ሁለተኛው በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ ለቅንጅት ራእዮች መሳካት ሲሉ ከፍተኛ መስዋእትነት  የከፈሉት የቅንጅት አባላት፣ ደጋፊዎችና ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሃገራቸን የሰፈነውን የተወሳሰበና አስቸጋሪ ሁኔታ ተረድተው በመፍትሄው ላይ ለመነጋገር የሚችሉበትን መንደርደሪያ ሃሳብ ለማቅረብ ነው። በሃገር ውስጥና በሃገር ውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ የጀመረውን "በሃገሬ ጉዳይ ያገባኛል" የሚል ጽኑ አቋሙን አጠናክሮ በእልህና በቁጭት የመፍትሄው አካል ሆኖ የሚቀጥልበትን ሁኔታ ለማጠናከር ነው። በተለይ የሃገሬ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ማንም ግለሰብ ገና ለገና በየቦታው አሉባልታ ከማሰራጨትና ስም ከማጥፋት በስተቀር ሌላ አቅምና ችሎታ የሌላቸውን ግለሰቦች የሚሉትን በመፍራት ትክክለኛ ነው የሚለውን እምነቱን ከመግለጽ እንዳይቆጠብ ለመደፋፈር ነው።  በተጨማሪም፣ ቁም ነገር ያለውን የሃገርና የህዝብ ጉዳይ ቅንጅት ወደ ጎን አድርጎ ግዜውን "በስራ የኮሰሱ በመንፈስ የረከሱ" ሃይሎች የሚያሰራጩትን በውሸት የተሞላ ተራ አሉባለታና ወሬ በማስተባበል እንዲያጠፋ ከሚያደርሱበት ግፊት ተላቆ ሁላችንም መሰረታዊ ወደ ሆኑ ጉዳዮች ፊታችንን ማዞር እንድንችል በማሰብ ነው።

የሚሳካልኝ ከሆነም፣ ለህዝብ ያላቸው ንቀት በስልጣን ላይ ካለው የወያኔ መንግስት ያልተናነሰና ምንም አይነት ይሉኝታ የማይሰማቸው በቅንጅት ውስጥና በቅንጅት ዙሪያ የበቀሉትን አውዳሚነት የተጣባቸውን ኋላ ቀር አመለካከቶች ለመሞገትና ማንንም በማይጠቅም አውዳሚ አካሄድ የሚንቀሳቀሱትን አካላት ፊታቸውን ገንቢ ወደ ሆነ

አቅጣጫ ለማስቀየር ነው። እነዚህ ሃይሎች በውስጣቸው የቀረ ፈሪሃ-ህዝብና ሃገር የማስቀደም ስሜት ካለ፣ በእዚህም ላይ ፍላጎቱንና ብቃቱን ከተላበሱ አርቲቡርቲውን አቁመው ፖለቲካ በአምክኖና በስልጡንነት የሚሰራበትን የጨዋ ድባብ እንዲቀላቀሉ ለመጋበዝ ነው። በተለይ ግን የእዚህ ጽሁፍ አላማ፣ ቅንጅት ከገባባት ቅርቃር እራሱን ማውጣት እንዲችል ሁላችንም በምንጋራው እውቀትና በምንግባባቸው አመለካከቶች ላይ የተመሰረተ የትግል ቃልኪዳናችንን የምናድስበትና ድጋፍ ማበርከት የምንችልበትን ሁኔታ ለማበረታት ነው።

ይህን ጽሁፍ እርስ በርሳቸው በተሳሰሩ አራት ክፍሎች የተከፈለ ነው።
እነዚህም፤

ሀ- በእዚህ ጽሁፍ ውስጥ ከምሰነዝራቸው ሃሳቦች ጋር ጥብቅ ትስስር ያላቸውን መሰረታዊ የቅንጅትን የፖለቲካ እምነቶች በቅድሚያ ማስቀመጥ፣

ለ- ከቅንጅት ገዥ የፖለቲካ እምነቶች በመነሳት፣ በእነዚህ የፖለቲካ እምነቶች መነጽር የቅንጅትን የውስጥ ችግር መመርምርና መፍትሄውን ማቅረብ፣

ሐ- ቅንጅትን ከስሙ ጀምሮ ለማጥፋት፣ በዋንኛነት በወያኔ ኢህአዴግና እንዲሁም በሌሎች የቅንጅትን መኖር በማይፈልጉ ሃይሎች የሚሰነዘርበትን ጥቃት በሚመለከት መደረግ የሚገባውን መጠቆም፣

መ--ከድርጅቱ ህልውና መከበር ጋር ተያይዞ መታየት የሚገባቸውን የድርጅቱን የወደፊት የፖለቲካ አቅጣጫዎችና ስራዎችን መጠቆም ናቸው።

## <u>1- ገዥ የፖለቲካ እምነቶች።</u>

በቅድሚያ ስለቅንጅት ገዥ የፖለቲካ እምነቶች ስጽፍ ሁሉም የድርጅቱ አባላት ደጋፊዎችና አመራራሮች በአንድ አይነት የግንዛቤ ደረጃና ስሜት የሚጋሩት፣ አንድ ወጥ የሆነ የፖለቲካ እምነት ማለቴ አይደለም። በአባለቱና በደጋፊዎቹ ብቻ ሳይሆን በቅንጅት አመራር ውስጥ ሳይቀር የኢትዮጵያን የፖለቲካ ችግር ለይቶ በማወቅና መፍትሄውን በመጠቆም የተለያዩ አመለካከቶች እንዳሉ ግልጽ ነው። ይህ ልዩነት ቅንጅት ከፈጠሩት የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና በድርጅቶቹ ውስጥ ተጽእኖ ማሳደር ከቻሉት ግለሰቦችና ቡድኖች የቆየ ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። ሌሎችን ልዩነቶች ትተን ስልጣንን በሚመለትከት ብቻ ያለውን ልዩነት ማየቱ ይበቃል። ግለሰቦች በአደባባይ ስለህዝብ የበላይነት ስለዴሞክራሲ ከሚናገሩት ውጭ ማንነታቸውን ከተግባራቸው መረዳት ይቻላል። ቀጥሎ የማቀረበው ግምገማ ባለፉት ሶስት አመታት ቅንጅትን ጠጋ ብየ ከማየት በግሌ የደረስኩበትን ነው።

"የኢትዮጵያ ፖለቲካ ችግር ወያኔ ነው። ወያኔ በቅንጅት ሲተካ የሃገራችን ችግር ይቃለላል" ብለው ከሚያስቡት አንስቶ; "ችግሩ መለስ ዜናዊና ጓደኞቹ ናቸው። እኔና ጓደኞቼ በእነሱ እግር ስልጣን ስንይዝ ችግሩ ይቃለላል" ብለው የሚያምኑ አሉ። "ችግሩ ወያኔ ነው ዋናው ነገር እሱን ማስወገድ ነው። ቅንጅትም ሆነ ማንም ቢያስወገደው ግድ የለኝም, ምንም ነገር ከወያኔ የማይሻል የለም" የሚሉ አሉ። በሌላ በኩል "ችግሩ በፓርቲዎች መለዋወጥ፣ በባለስልጣኖች መቀያየር ሳይሆን ለፖለቲካው ችግር ተቋማዊ (institutional) መፍትሄ በመስጠት የሚቃለል ነው ብለው የሚያምኑ" አሉ ።

በበኩሌ እንደታዘብኩት በሃገር ቤትም ይሁን ከሃገር ውጭ የሚገኘው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ለቅንጅት ድጋፉን የሰጠው ቅንጅት በሃገራችን ውስጥ ህዝብን የስልጣንና

የገዛ ሕይወቱ ባለቤት ለማድረግ እወስዳቸዋለሁ ላላቸው መሰረታዊ ለውጦች ነው። ስለሆነም የድርጅቱ ገዥ የፖለቲካ እምነት "ለሃገራችን የፖለቲካ ችግር መፍትሄው መዋቅራዊና ተቋማዊ ለውጥ ማድረግ ነው" ከሚለው ሃሳብ ውጭ ሊሆን አይችልም። ባለፉት ሶስት አመታት የኢትዮጵያ ህዝብ በቅንጅት አመራር መስዋእትነት የከፈለለትና የቅንጅትም መሪዎች በጋራ ወስነው በጋራ ለእስር የተዳረጉበት ጉዳይም ዴሞክራሲን በሃገራችን ለመትከል የነጻ ተቋማት መኖር አስፈላጊ ነው ብለው በማመናቸው ነው። ይህንን እምነት የሚጻረር፣ ግዜና አጋጣሚ እየጠበቀ በአንድ አንድ የቅንጅት አመራርና ደጋፊዎቹ የሚሰራጨው የተለየ አመለካከትና የሚፈጸመው ድርጊት ሁሉ ድርጅቱን አይወክልም ።

ቅንጅት ሰላማዊና ህጋዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ የተቋቋመ ድርጅት ነው። "በሃገራችን ውስጥ የመንግስት ስልጣን በየወቅቱ ህዝብ በሚሳተፍበት ነጻና ዴሞክራሲየዊ ምርጫ አብላጫውን ድምጽ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት/ድርጅቶች መያዝ አለበት" ብሎ ያምናል። ቅንጅት በእዚህ መንገድ ተወዳድሮ በህዝብ አብላጫ ድምጽ ካገኘ ሰልጣን ለመያዝ፣ በሚይዘውም የአምስት አመታት የስልጣን ዘመን ውስጥ ምን መስራት እንደወሰነ ዝርዝር ፖሊሲዎቹን በምርጫ ማኒፌስቶ ያስቀመጠ ብቸኛ ድርጅት ነው። በእዚህ እምነት ተመርቶ በግንቦት 1997 ብሄራዊ ምርጫ ተሳትፎ የሀገራችንን የዴሞክራሲ ምርጫ መሰረታዊ ችግሮች ምን እንደሆኑ ከተጨባጭ ተመክሮ ለማጤን የቻለ ድርጅት ነው።

እንደተባለው ቅንጅት በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ስልጣን ለመያዝ የተቋቋመ ድርጅት ቢሆንም ከሌሎቹ በሃገራችን ከሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች የሚለየው ቁም ነገር አለ። ይህም የፖለቲካ ድርጅቶች የመንግስት ስልጣን ለመያዝ ከሚያደርጉት ጥረት ጎን ስልጣን የሚይዙበት አግባብ እራሱ ትልቅ ትረጉም ሊሰጠው የሚገባ የፖለቲካ ጉዳይ ነው ብሎ ማመኑ ነው። በእዚህም እምነቱ በሃገራችን ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የስልጣን ሽግግር የሚደረግበት ሂደት የሃገራችንን የፖለቲካ ችግር ለመፍታት ቁልፍ ነው ብሎ ያምናል። ይህንን ችግር ማቃለል የማህበራዊና የኢኮኖሚ ችግሮቻችንን ለማቃለል በር ከፋች እንደሚሆን ቅንጀት ደጋግሞ አስገንዝቧል።

ይህ ማለት ህዝብ በነጻ ድምጹን ሰጥቶ፣ ድምጹ ተከብሮ ስልጣን ላይ የሚወጣው የፖለቲካ ፓርቲ የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ቢሆን ቅንጅትን አያሳስበውም። ከእነዚህ ፓርቲዎች መሃል አንዱ እራሱም ወያኔ ሊሆን ይችላል። የኢትዮጵያ ህዝብ የመብት፣ የነጻነት፣ የብልጽግና ዋስትና በአንድ ወቅት ህዝብ ያመነውን የፓለቲካ ድርጅት ለስልጣን ማብቃት አይደለም። ለስልጣን የበቃ ድርጅትን ቃሉን ጠብቆ ባይገኝ ከስልጣን ማባረር መቻሉ ላይ ነው። የህዝብ የዘለቄታ ጥቅም የሚከበረው በሃገር ውስጥ በሚጣለው ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንጅ በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ወይም መሪዎች ቃልና ተስፋ ላይ አይደለም። ቅንጅት ለደጋፊዎቹና ለተቀረውም የሃገሪቱ ህዝብ በተለያዩ ግዚያት ይህን ግልጽ አድርጓል። ምን ያህሎቻችን ይህንን መልእክት በሚገባ ሰምተናል? ቅንጅት ስልጣን እንዲያዝ የምንፈልገውን ያህል ህዝብ ባልፈለገው ሰአት የምንወደውንም ቅንጅትን ህዝብ ከስልጣን ማባረር የሚችልበት የፖለቲካ ስርአት በሃገራችን መገንባት አስፈላጊ ነው ብለን ምን ያህሎቻችን እንደምናምን ማወቁ አስቸጋሪ ነው። እንዲህ አይነቱን አመለካከት አጥብቅን ስንይዝ ብቻ ነው፤ በሃገራችን ለአንዴና ለሁልግዜ አምባገነንነትን በማጥፈት፣ ዘለቄታነት ያለው የሰላም፣ የነጻነትና የብልጽግና

ህይወት በሃገራችን መገንባት የምንችለው። ቅንጅት የሚታገለው ለስልጣን የሚያበቃውን እድል የሚፈጥርለት አንድ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በሃገራችን እንዲካሄድ ብቻ አይደለም። ሁሌም የሚካሄዱ ምርጫዎች ዴሞክራሲያዊ እንዲሆኑ ነው። የስልጣንን ህጋዊ፣ ማህበራዊና ሞራላዊ ቅቡልነት ሁሌም ከሰላማዊ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲመነጭ ለማድረግ ነው።

በአንድ ሃገር ላይ ሰላማዊ፣ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተደረገ ማለት በእዛ ሀገር ላይ አምባገነንነት አበቃለት ማለት አይደለም።[1] እንደወያኔ በጠመንጃ ሃይል ስልጣን የያዙቱ ብቻ ሳይሆኑ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ስልጣን ያገኙትም ጭምር፣ በሌላ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሲሸነፉ ከስልጣን አልወርድም የሚሉ አምባገነኖች መሆን እንደሚችሉ በቅርቡ ኬንያ ውስጥ የተከሰተው ችግር ጥሩ ምሳሌ ነው። ተመሳሳይ ችግሮችም በምስራቅ አውሮፓ ሃገሮች ውስጥ እየተከሰተ ነው። ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በሀገራችን መደረግ አለበት የሚል ትግል አድርጎ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ስልጣን የያዘው የኬንያ ተቃዋሚ ፓርቲ በተራው በሌላ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በተቃዋሚው ሲሸነፍ ከስልጣን አልወርድም በማለት ልክ ወያኔ በ1997 የፈጠመውን ወንጀል በሃገርና በህዝብ ላይ ሲፈጽም አይተናል። በውጭ መንግስታትና በአለም አቀፍ ሚድያው ሀገራችን የምትታይበት ደረጃ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ ለወያኔ ወንጀል ትኩረት አልሰጡትም እንጂ ምርጫ 97ን ተከትሎ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የመለስ ዜናዊ ድርጅት የፈጸመው ግፍ የኬኒው የኪባኪ ፓርቲ ከፈጸምው አጅግ የከፋ ነው።

ስለእዚህም ነው ቅንጅት "በሃገራችን ስልጣን ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንዲተላለፍ የሚያደርገው ትግል አንዴ ብልጭ ብሎ ድርግም" የሚል ምትሃት መሆን የለበትም የሚለው። በሃገራችን እንደታየው የስልጣን ሽግግሩ ወግ ቀርቶብን፣ በግንቦት 97 የምርጫ ወቅት አይተነው የነበረው የዴሞክራሲ ጭላንጭል ብልጭ ብሎ ድርግም ያለው በወያኔ በጎ ፈቃድ የተገኘ እንጂ የመዋቅራዊና የተቋማዊ ዋስትና ያልነበረው በመሆኑ ነው። በሃገራችንም ሆነ በኬንያ የሆነው ሁሉ የሚያስተምረን፣ "ዴሞክራሲን፣ ሰላምንና ህጋዊነትን የሃገራችን ፖለቲካ ቋሚ መገለጫዎች ማድረግ የሚቻለው ከማንኛውም ነገር በፊት ቅድሚያ፣ ለመንግስትና ለመሪ ለውጥ ሳይሆን ለስርአት ለውጥ መሆን አለበት" የሚለው የቅንጅት አቋም ፍጹም ትክክለኛ መሆኑን ነው።

የቅንጅት ትግል በዴሞክራሲ ስም ሌላ አምባገነን በህዝብ ላይ እንዳይጫን አልሞ የተነሳ ነው። በዴሞክራሲ እየማሉና እየተገዘቱ የዴሞክራሲው ሂደት ደጃፋቸው ላይ ማንኳኳት ሲጀምር "እኛን እኮ አይመለከተንም" የሚሉ ድርጅቶች ክበብ አባል የመሆን ፍላጎት ቅንጅት የለውም። ዴሞክራሲያዊ ስርአት በሃገራችን እንዲተከል ከልብ የሚጨነቁና አምረው የሚታገሉ ሁሉ፣ ይህ አይነቱ ስርአት ሲጠናከር፣ ታግለው ያቆሙትንና

---

[1] በተመሳሳይም በአንድ ድርጅት ውስጥ አንዴ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተደረገ ማለት ድርጅቱን እንዳሻቸው ለማድረግ የሚችሉ፣ የተነሳበትን ዴሞክራሲያዊ መሰረት የሚያስለቅቁት መሪዎችና አባላት አይኖሩትም ማለት አይደለም። በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ በምርጫ መሪ ሆነው በሂደት ግን እራሳቸውን የድርጅት ፈላጭ ቆራጭ ያደረጉ መሪዎች ሞልተዋል። ሩቅ ሳንሄድ መንግስቱ ሃይለማሪያምና መለስ ዜናዊ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። ሃገርንና ድርጅትን ከእንዲህ አይነቶቹ አምባገነኖች መካላከል የሚቻለው፣ በግለሰቦቹ ጥሩነት በመተማመን፣ በመለማመጥ በመማጸን ሳይሆን የሃገርና የድርጅት ዴሞክራሲ ባህርያት ሊያጠፉ የሚችሉትን አደጋዎች በሚገባ አጥንቶ መከላከያቸውን በማዘጋጀት ነው። ለዴሞክራሲ ዋሰትና በዘላለማዊ ዘበኝነት (eternal guardian) መቆም የሚችሉ ደንቦች ስርአቶችና ተቋሞች በመመስረት ነው። የእነዚህ ተቋማት ነጻነት እንዳይገሰስ ህለውናቸው እንዳይደፈር ዜጎችና የድርጅት አባላት ሳይታክቱ ዘላለማዊ ዘብ ሆነው እንዲቆሙ በማድረግ ነው።

ስርአቱ እንዲጠናከር የታገሉለትን ሳይቀር፣ አጥፍተው ከተገኙ፣ ከስልጣን የሚያባርር፣ የሚቀጣና መናኛ አድሮጎ የማስቀረት ጉልበት እንዳለው መረዳት አለባቸው። በስርአት መልኩ ከታየ ዴሞክራሲም እንደ ፍትህ እውር ነው። አድሎ አያወቅም። ሁሉንም በእኩልነት የሚያይና የፖለቲካ ዳኝነት ለሁሉም በእኩልነት የሚሰጥበት የፖለቲካ ሂደት ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ የደረሰበት የፖለቲካ ብስለትና ዝግጁነት፣ በዜግነቱና ለነጻነቱ በታሪኩ የከፈለው መስዋእትነት፣ በላዩ ላይ የተከመረበት በድህነትና በመብት ገፈፋ የተሞላ የመከራ ህይወት የጠራና የበቃ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ባለቤት ሊያደርገው የግድ ይላል። ትግሉ በከፍተኛ መስዋእትነት ህዝብ የሚያገኘውን ዴሞክራሲያዊ ድል በቀላሉ በሌሎች አምባገነኖች መልሶ እንዳይቀማ ለማድረግ ጭምር ነው። የአምባገነንነትን አሰከፊ የፖለቲካ አዙሪት ቋሚነት ባለው ዴሞክራሲያዊ ሂደት መተካት ነው። ምርጫ 1997 ያሳየው ቅንጅትም የሚያምነው ይህንን ነው እላለሁ። ባለፉት ሁለት አመታት የሃገሩ ጉዳይ አሳሰቦት በአለም ዙሪያ የተንቀሳቀሰው ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊና የቅንጅት ደጋፊ የሚያምነው ይህንኑ ነው። ብዙዎቻችንም በላፉት ጥቂት አመታት ቅንጅትን ከሌሎች ድርጅቶች ለይተን በዋንኛት የደገፍነው በዴሞክራሲ ጥያቄ ላይ ጥራት ያለው አመለካከት የተላበሰ ድርጅት መሆኑን አምነን ነው።

ይሁንና በሂደት እንደታየው በቅንጅት ውስጥ በእዚህ መሰረታዊ ጉዳይ ላይ አንድ ወጥ አቋም እንደሌለ ግልጽ እየሆነ መጥቷል። መሪዎቻችን ለእስር ከተዳረጉ በኋላ በዋንኛነት በውጭ በተደረገው የድርጅቱ እንቅስቃሴ ላይ የተከሰተው ችግር ከእዚሁ መሰረታዊ ጉዳይ ጋር የተሳሰረ ነው።[2] ቅንጅት በማኒፌስቶው ያስቀመጣቸው የዲሞክራሲ፣ የግልጽነትና የተጠያቂነት መሰረታዊ እሴቶች ሌላውን እንጂ እኛን አይገዛንም የሚሉ ጥቂት ኋላቀር ሃይሎች የድርጅቱን እንቅስቀሴ ለማኮላሸት የላደረጉት ጥረት አልነበረም። ይህ ጥረት አሁንም አላቆመም። መሪዎቻችንንም ከእስር ከተፈቱ በኋላ በመሃከላቸው

---

[2] በውጭ የተደረገው እንቅስቃሴ የገጠመው አንድ መሰረታዊ ችግር ከዴሞክራሲ ባህል ጋር የተሳሰረ ነው። ለረጅም ዘመን በየሃገሩ በተጀመሩ አንቅስቀሴዎች ውስጥ በመግባት በተለያዩ መንገዶች የሃለፊነት ቦታውን ይዘው የኖሩት ጥቂት ግለሰቦች ነበሩ። ይህ ሁኔታ እየዋለ እያደረ እነዚህ ግለሰቦች ያለእነሱ ፋቃድ ቁጥጥርና ቡራኬ ምንም አይነት እንቅስቀሴ መደረግ አይችልም የሚል እምነት እንዲይዙ አድረጓቸዋል። ሆኖም ከቅንጅት መፈጠር ጋር የብዙሃንን ተሳትፎ ያለበት የፖለቲካ ሂደት በሃገራችንን ሲከሰት፣ የእዚህ ሂደት ግፊትም በውጭ ሃገር ተመሳሳይ የብዙሃንን የፖለቲካ ተሳትፎ አስከተለ። የእዚህ የብዘሃን የፖለቲካ አንቅስቃሴ ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀትና አሰራርን ይዞ ከመሄድ ውጭ ሌላ መጓዣ አቅጣጫ አልነበረውም። በአንድ አንድ ቦታዎች የቅንጅትን የድጋፍ ድርጅቶች ዴሞክራሲያዊ አድርጎ ለማዋቀር የተደረገውን አንቅስቃሴ ቀደም ብለው የውጭውን እንቅስቀሴ በመኖፖል በበላይነት በተቆጣጠሩት ግለሰቦች ላይ የተሰነዘረ ጥቃት ተደርጎ መወሰድ ጀመረ። በስፋት የመጣውን፣ ፖለቲካ ውስጥ ገብቶ የማያውቀውን ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ አስተሳሰብና ብስለት ግምት ውስጥ ያስገባ አደረጃጀት በማዘጋጀትና በማቀፍ ቅንጅት ለማጠናከር ከመሞከር፣ አዲስ የመጣውን የሰው ሃይል የተለያዩ ምክንያቶች በመስጠት ለማራቅ፣ በተለይ በተደራጀ መልኩ እንዲንቀሳቀስ አለመፈለግ ታየ። ስንት አመት ስንታገል ኖረን በዴሞክራሲ ስም አዲስ ለመጡ ግለሰቦች ቦታ እንለቃለን፣ አልፎ ተርፎ ሌላው ይመራረጥ እንጂ እኔን የመሰለ ለሀገር አሳቢና አዋቂ እንዴት ለምርጫ ቅረብ እባላለሁ የሚሉ ደፋሮች ታዩበት። ትግሉ በውጭ እንቅስቀሴ ውስጥ በአንድ አጋጣሚ የተያዘን የበላይነት መከላከል እንጂ በሃገራችን የሚካሄደው የዴሞክራሲ ትግል የትኛው አሰራርና አደረጃጀት ያግዘዋል የሚለው አልነበረም። በአለንበትም ወቅት በቅንጅቱ አመራር ውስጥ የተፈጠረውን ልዩነት በማራገብ በሚፈጠረው መከፋፈል ያችኑ የተለመደች የበላይነታቸው የተረጋገጠበትን የውጭ ሃገር የፖለቲካ ጉልት ይዘው ለመቀጥል የሚፈልጉ ግለሰቦች በየሃገሩ ሲንቀሳቀሱ በማየት ላይ ነን። ስለእዚህ ነው፣ ስለቅንጀት እያወሩ ቅንጅትን እንደግፋለን እያሉ፣ የቅንጅትን የውጭ እንቅስቃሴ ብዙሃንን አካቶ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለማደራጀት የተደረገውን ሙከራ ሲቃወሙና ዛሬም በእዚሁ እምነታቸው ለመቀጥል የሚፈልጉ በሙሉ መሰረታዊ የሆኑትን የቅንጀት የፖለቲካ እምነቶች አያውቋቸውም ወይም እይጋሩም የምለው።

የተከሰተው ችግር በሃገራችን ቁልፍ የሆነው የፖለቲካ ችግር የቱ እንደሆነ በማወቅና ባለማወቅ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው።

ከእዚህ በላይ የሰፈሩትን መሰረታዊ ቁምነገሮች ወደ ጎን በማድረግ፣ ቅንጅት ስለራሱ ድርጅት የውስጥ ችግርም ሆነ በሃገሪቱ ውስጥ ስላለው የፖለቲካ ችግር መፍትሄ ማፈላለግ አይችልም። መሰረታዊ በሆነው ጉዳይ ላይ የጠራ አመለካከት አለመኖር ቅንጅትን ለገጠሙት ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች መልስ መስጠት እንዳይቻል፣ ግልጽ አቅጣጫ አስቀምጦ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ስራዎች በቅደም ተከተል ደርድሮ ድርጅቱን ማንቀሳቀስ እንዳይችል አድርጎታል የሚል ስጋት አለኝ።

*<u>2- በቅንጅት አመራር ውስጥ የተነሳው ቀውስና እና መፍትሄው።</u>*

ቅንጅት በሃገራችን ትልቁ የፖለቲካ ጥያቄ  ስልጣን የሚያዝበትን ሂደት ዴሞክራሲያዊ ማድረግ ነው ብሎ እንደሚያምን ግልጽ አድርጌያለሁ። በስልጣን ላይ በሚገኘው ገዥ ክፍል ይሁን፣ ይህንን ገዥ በሚቃወመው ሰፊ የፖለቲካ ልሂቅ አካባቢ ስልጣን ይገባናል የሚል ግጭት እንጂ ስልጣን የምንይዝበት መንገድ ዴሞክራሲያዊ ሊሆን ይገባዋል የሚል እምነት እንደሌለ ግልጽ ነው። ወያኔ በ1997 ምርጫ ሽንፈት ከገጠመው በኋላ በግድያና በአፈና በስልጠን ላይ መቀጠሉ ለእዚህ ማረጋገጫ ነው። ወያኔ/ኢህአዴግ፣ "ማንንምና ምንንም ፍጭ፣ ስልጣኑን አምጭ" በሚል ብሂል የሚመራ ድርጅት እንደሆነ አይተናል።

በተመሳሳይም የበርካታ ተቃዋሚ ፓርቲ ድርጅቶችና መሪዎች ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ስልጣን ከያዘ ድርጅት ጋር የተለያዩ ስበቦች በመስጠት ስልጣን ተካፍለው፣ በፓርላማ ውስጥም ቢሆን አብረው ለመጓዝ መሞከራቸው የወያኔ መንግስት ስልጣን የያዘበት ሂደት የሚያሳስባቸው እንዳልሆነ የሚያረጋግጥ ነው። በተለይ ዛሬ በፓርላማ ውስጥ የሚርመሰመሱት ተቃዋሚዎች ለወያኔ ህገወጥ መንግስት ህጋዊ ሽፋን በመስጠት፣ በተለይ በዲፕሎማሲ መስኩ ሊደርስበት ይችል ከነበረው ጫና ተከላክለውለታል። በእዚህ ድርጊታቸው የኢትዮጵያን ህዝብ የዴሞክራሲ ትግል ምን ያህል እንዳሻጠሩት ታሪክ ወደፊት የሚዘግበው ይሆናል።  እነርሱም እድል ቢያገኙ ወያኔ ስልጣን ይዞ መቀጠል በቻለበት መንገድ ለመቀጠል ህሊናቸውን የማይቆረቁራቸው መሆናቸውን የሚያሳይ ነው። በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈነው የፖለቲካ ሁኔታ የከፋ አምባገነናዊነት የነገሰበት እንደሆነ እየታወቀ፣ ከወያኔ ጋር እየተሞዳሞዱ የቀጠሉት ወይም የወያኔ ህገወጥ የስልጣን ባለቤትንት ወደጎን አድርገው የፖለቲካ ሂደቱ ጤነኛ ይመስል አይን አቸውን ጨፍነው የሚንቀሳቀሱት በሙሉ ፍላጎታቸው ዴሞክራሲያዊ ሂደት በሃገራችን መፍጠር ሳይሆን፣ ሲቻል ሰልጣንን እንደወያኔ በሞኖፖል መያዝ፣ ካልተቻለም ሰልጣንን ከሌላው ጉልበተኛ ጋር ተካፍለው ከመኖር ያለፈ ህልም እንደሌላቸው የሚያሳይ ነው።

ቅንጅት የወያኔን ህገወጥ የስልጣን አያያዝ ሲቃወም በምርጫው አሸንፌያለሁና ስልጣን ይገባኛል በማለት አልነበረም። በምርጫው አሸንፏልና ይህንንም ቢል መብቱ ነበር። ከምርጫው በኋላ የሃገሪቱን ችግር ለመፍታት የብሄራዊ አንድነት መንግስት ይቋቋም የሚለውን ሃሰብ ሲደግፍ፣ የድርጅቱ መሪዎች ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር የሚኒስቴርነት ስልጣን የሚጋሩበት የግል የስልጣን ሱሳቸውን ለማርካት የፈለጉበት ሁኔታ ለመፍጠር አልነበረም። በመጨረሻም፣ የቅንጅት መሪዎች  ፓርላማ አንገባም ሲሉ ስልጣን ስላላገኙ

በማኩረፍ አልነበረም። በወያኔ ህገወጥ ፓርላማ ውስጥ ገብተው ከረቫታቸውን አንጀርገው ወያኔ እንደ ወሃ ቢንቢ እንዳሻው በሚለቀውና በሚዘጋው የመናገር መብት ትርጉምና ፋይዳ የሌለው ንግግር መናገር የማይችሉ በመሆናቸው አልነበረም።

ቅንጅት ከምርጫ 97 በኋላ በተከታታይ የወሰዳቸው እርምጃዎች ከማናቸውም ጉዳይ በላይ ባለንበት ታሪካዊ ወቅት በሃገራችን ስልጣን የሚያዝበት ሂደት ስልጣን ከመያዙ በላይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የሚል እምነት እንዳለው የሚያሳይ ነው። ለሰላማዊነትና ህጋዊነት የሰጠው አጽንኦት የእዚህ እምነቱ ውላጅ ነው። ቅንጅት ሁሉን የሃገሪቱን የፖለቲካ ሃይሎች ያካተተ፣ በምርጫ የተሳተፉትንና ያልተሳተፉትን ጨምሮ፣ የብሄራዊ አንድነት መንግስት እንዲመሰረትና በኋላም የተወሰኑ ቅድመ-ሁኔታዎች አስቀድሞ ፓርላማ ለመግባት ፈቃደኛነቱን የገለጸው፣ በሁለቱም መንገድ ተሄዶ ውጤቱ በሃገራችን የተጀመረውን ዴሞክራሲያዊ ሂደት የሚያጠናክር እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባት የሚያስችል እድል ይገኛል የሚል እምነት ስለነበረው ነው። በተጠቀሱት መንገዶች በመሄድ በሃገራችን በ97ቱ ምርጫ ጋር የተጀመረውን ዴሞክራሲያዊ ሂደት ስር እንዲሰድ የሚያደርጉ፣ ዴሞክራሲያችን በድርጅቶችና በመሪዎች በጎ ፈቃድ የሚሰጥና የሚከለከል ሳይሆን ዜጎች በመብት ደረጃ የሚገባቸው መብት መሆኑ ታውቆ ይህንን መብት በገለልተኛነት የሚያስከብሩ የነጻ ህገ-መንግስታዊ አካላት መገንባት ይቻላል በሚል አምነት ነው። ቅንጅት ከሁሉንም ነገር በላይ ትኩረቱ ከማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ ነጻ የሆነ የፍትህ አካል፣ የሃገር መከላከያ የፖሊስና የጸጥታ ሃይል፣ ነጻ ሚድያ፣ ነጻ የምርጫ ቦርድ በሃገራችን እንዲኖር አጥብቆ ታግሏል። በመቶ ሽህ የሚቆጠሩ የቅንጅት አባላትና የድርጅቱ መሪዎቹ ከፍተኛ መስዋእትነት ለመክፈል የተገደዱት በእዚህ እምነታቸው የተነሳ ነው።

ቅንጅትን እንደ ድርጅት በምናጤንበት ግዜ ከእዚህ በላይ የጠቀስናቸውን የድርጅቱን እምነቶችና ለእነዚህ እምነቶቹ በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ በሚገኙ አባላቱና ደጋፊዎቹ የተከፈለውን መስዋእትነት ግምት ውስጥ በማስገባት መሆን ይኖርበታል። በተለይ ባለፉት ሁለት የመሪዎቻችን የእስር ዘመናት በሃገር ውስጥና በሃገር ውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ባገኘው አጋጣሚ የቅንጅት ስምና አርማ ከፍ አድርጎ ያውለበለበው፣ ብርዱ ከዜሮ በታች በወረደበት ሰአት እጅን አውጥቶ ለሰአታት ምስላቸውን ይዞ መቆም ሲያቅተው በአንገቱ ላይ በክር አስሮ በቁር የተሰቃየው ቅንጅት ለቆመላቸው ህዝብንና ሃገርን ይጠቅማሉ ብሎ ላመነባቸው ራእዮች ነው። ይህ ሁሉ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ የቅንጅት መሪዎች የእዚህ ራእይ ተሸካሚዎች አይደሉም ብሎ ቢያስብ እንኳን በተከታታይ አለምን ያስገረመ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ቀርቶ ለአንድም ቀን ከቤቱ አይወጣም ነበር።

በሃገር ደረጃ ለህግ የበላይነት፣ ለዜጎች ነጻነት መከበር፣ ከግለሰቦችና ቡድኖች ፍላጎትና ቁጥጥር ውጭ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲመሰረት ግንባር ቀደም ሚና የሚጫወት ድርጅት፣ የገዛ ድርጅቱን ተመሳሳይ በሆኑ እሴቶች ዙሪያ መገንባት የማይችል ከሆነ ከተቀሩት ለስልጣን እንጂ ስልጣን ስለሚያዝበት መንገድ ብዙ እንደማይጨነቁት የሃገራችን የስልጣን ጥመኞች የሚለየው አይኖርም።

ከምርጫው በፊትና በኋላ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ጥቂቶቻችን በእዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ብለናል። "አንድ ድርጅት በሃገሪቱ ላይ ለመገንባት ቃል የሚገባውን ዴሞክራሲያዊ

የፖለቲካ ስርአት እውን ማድረግ ወይም አለማድረግ መቻሉን ከፓርቲው ድርጅታዊ ባህርይ መረዳት ይቻላል። ከእባብ እንቁላል እርግብ መጠበቅ እንደማይቻል ሁሉ፣ የራሱን ህግና ስርአት የማያከበር፣ የድርጅቱን አባላት መብትና ነጻነት የማያስጠበቅ፣ ዴሞክራሲያዊና ስልጡን የሆነ የፖለቲካ ባህል በድርጅቱ ውስጥ እንዲያብብ ማድረግ የማይችል ድርጅት፣ ራሱን ከሙስና ነጻ ማድረግ የማይችል ድርጅት፤ በሃገር ደረጃ ስልጡንነትን፣ ጨዋነትን፣ ሰለማዊነትንና ህግን የሚያከበር፣ ከአፈናና ከሙስና ነጻ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መገንባት ከቶውኑ አይችልም" ብለን በቃልም በጽሁፍም ወትውተናል።

"ማንኛውንም ድርጅት ህዝብ ደግፎ ለስልጣን ከማብቃቱ በፊት መሰረታዊ በሆኑ የዴሞክራሲያዊነት መስፈርቶች ለክቶ ሊደግፈው ያሰበው ድርጅት በሚገባ እነዚህን መስፈርቶቹን ማሟላቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል። ክቡር የሆኑትን ዴሞክራሲያዊ እሴቶችን በሃገር ላይ በስራ ከማዋል ይልቅ በዴሞክራሲ እምነቶች ዙሪያ በተሰባበሰቡ አባላት በተሞላ ድርጅት ውስጥ በተግባር ለመተርጎም ቀላል ነው። ይህንን በቀላሉ ሊከናወንና ከግለሰቦች በተለይ ከድርጅት መሪዎች ፍላጎት ውጭ ሌላ ትልቅ ነገር የማይጠይቅን እጅግ አነስተኛ ድርጊት ማከናወን ሳይችሉ፣ ስልጣን በተያዘ ግዜ ስለሚገነባ የማርና የወተት ዴሞክራሲያዊ ሃገር ለሚያወሩት ሁሉ መልሳችን ሞኛችሁን ፈልጉ መሆን አለበት።" በማለት ደጋግመን አሳስበናል። ደግነቱ በምርጫው ወቅትና ከምርጫው በኋላ በሃገር ውሰጥና ከሃገር ውጭ የሚገኘው አብዛኛው የኢትዮጵያ ያሳየው የፖለቲካ ብስለት፣ በተለይ ስለዲሞክራሲና ለዲሞክረሲ ተቋማት መኖር የያዘው ግንዛቤ በህዝብ፣ በሃገርና በዴሞክራሲ ስም እየማሉና እየተገዘቱ አላማቸው እንደወያኔ ስልጣን ላይ ወጥቶ በህዝብ ላይ ለመከመር የሆኑትን የሚያንቀሳቀስ አይደለም።

ወደ ቅንጅት ስንመለስ መሪዎቻችን ከእስር ከተፈቱ በኋላ በድርጅቱ ውስጥ በአደባባይ የተከሰተው ቀውስ አይተናል። ብዙዎቻችን ግን ይሆናል ብለን ያሰብነው ሌላ ነበር። "የጋራ እስር የበለጠ የመንፈስ አንድነት ይፈጥርላቸዋል፣ በጋራ ወስነው በጋራ ተሰቃይተው በጋራ ከእስር በመፈታታቸው ከመቼውም በላይ በወንድማማችነትና እህትማማችነት ስሜት ይተሳሰራሉ። በተለይ ከመርጫ 97 በኋላ በሃገረችን ህዝብና በራሳቸውም ላይ ከተደረሰባቸው ስቃይና እንግልት ተነስተው በፖለቲካ አመለካከታቸው የበለጠ ተቀራርበው ጥልቀትና ጥራት ያለው አመራር ይሰጡናል" ብለን ሁላችንም ጠብቀን ነበር።

ትግሉ በሃገር ቤትና ከሃገር ውጭ የገጠመውን የአመራር ችግር በሚገባ ለመረዳት ቅርበት ያለን ግለሰቦች የመሪዎቻችን ከእስር መውጣት የሚኖረውን ጠቀሜታ በመግለጽ በጋራ ሳይለያዩ የሚፈቱበትን ማናቸውንም ሁኔታ በጥሞና እንዲያስቡበት የሚማጸን ደብዳቤ እስር ቤት ድረስ እንዲገባ አድረገናል። ደብዳቤው ላይ የሰፈሩት ቁምነገሮች ሁሉም በጋራ አንድ አይነት አቋም ይዘው በአንድ ላይ እንዲወጡ ለማድረግ የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል።[3] ደብዳቤው በዋንኛነት የጠየቀው በአስቸኳይ ተፈተው የድርጅቱን

[3] ይህ ደብዳቤ በዶክተር ሞገስ ገብረማሪያምና በእዚህ ጽሁፍ ጸሃፊ አመካይነት የተጻፈ ነው። በሽማግለዎቹ አማከይነት ከወያኔ ጋር ስለመፈታት የመጨረሻው ድርድር በተደረገበት ወቅት፣ መሪዎቻችን በመፈቻው ሰነድ ላይ የተለያያ አቋም መያዛቸውና መከፋፈላቸው ተነገረን። አልፎ ተርፎም አብዛኛዎቹ በወያኔ የቀረበውን ሰነድ ፈርመው ለመውጣት ዝግጁ መሆናቸውን፣ ይህን የሚያደርጉት ከእስር ለመውጣት ሳይሆን በመውጣት የዴሞክራሲ ትግሉን የበለጠ ለመግፋት ይቻላል የሚል ምክንያታቸውን ደርድረው ያስረዱ ሲሆን፣ የተቀሩት ጥቂቶቹ የሞራልና የህግ ጥያቄ

አመራር ተረክበው ትግሉ ባስቸኳይ የሚንሰራራበትን ሁኔታ በጋራ እንዲያመቻቹ ነበር። በተለይ ከእስር ቤት ሁሉም የድርጅቱ መሪዎች የተስማሙበትን ስርአት የጣሰ የተዘበራረቀ መመሪያና መልእክት መውጣት መጀመሩ የመሪዎቻችንን አንድነት የሚያናጋና ትግሉን ክፉኛ የሚጎዳ መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ፤ የመሪዎቻችን መፈታት አማራጭ ያልነበረው ጉዳይ ነበር። በተለይ በውጭ ትግሉን እንዲመሩ ሃላፊነት በተሰጣቸው ጥቂት ግለሰቦች አማካይነት፣ በዋንኛት በሃገር ቤት ውስጥ ትግል ለማድረግ የተጀመረውን ጥረት የሚያኮላሽ የገንዘብ እቀባ መፈጸሙ፣ ትግሉን ሃገራዊ መሰረት በማሳጣት በውጭ ሃገሮች የሚካሄድ እርባና የሌለው እንቅስቃሴ እያደረገው መምጣቱ አጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነበር። ይህም መሪዎቻችን በአንድነት ከእስር ወጥተው የመሪነት ሀላፊነታቸውን በአስቸኳይ ተረክበው፣ የከፈሉት መስዋእትነት የሰጣቸውን የሞራል የበላይነት በመጠቀም የተበላሸውን በማረም፣ የተጣመመውን በማቃናት ትግሉን እንዲቀጥሉ እንድንመኝ አደረገን። ይህ ሁሉ ምኞት ግን ሳይሆን ቀረ። የተከሰተው የድርጅቱን አባላትና ደጋፊዎች ሃዘን ያበረታ፤ ልብ የሰበረ ጉዳይ ሆነ።

ብዙዎቻችን ይህ ይሆናል ብለን ፈጽሞ ያልጠበቅነው በመሆኑ ምን ማለትና ምን ማድረግ እንደሚገባን ሳናውቅ ግራ እንደተጋባን ወራት አለፉ። በተለይ ለድርጅቱ ቅርበት ያለን ግለሰቦች ከምናውቃቸው እውነታዎች ጋር የሚጋጩ አስተያየቶች ሲሰጡ፣ መግለጫዎች ሲወጡ የማናውቀው ነገር ይኖራል ከሚል ስጋት ዝምታን መረጥን። በተለያዩ ወሳኝ የታሪክ ወቅቶች የፖለቲካ ልሂቁ አንድነቱን ማጥበቅ ባለመቻሉ የተነሳ የህዝብን መከራ አራዝሞታልና ለአንድነት መቆም አለብን ከሚል እውነተኛ ጭንቀት፣ ህሊናችንንም በቅንጅት ውስጥ እንዲህ ያለ ችግር ሊከሰት አይችልም በሚል ቀቢጸ-ተስፋ እንዲያምን አድርግን ተንሳፈን ቀረን። የምናያቸውና የምንሰማቸውን ጥፋቶች "ግለሰቦችና ቡድኖች መጥፎ ስላሰቡ ሳይሆን ከመረጃ እጦት፣ በአካልም በመንፈስም በመድከም፣ ከበሽታና ከእስራት ጉዳት ማገገም ካለመቻል፣ ረጋ ብሎ ለማሰብ እደል

---

በማንሳት ፈርመን መውጣት የለብንም ማለታቸው ሰማን። እነዚህ የየራሳቸው ምክንያቶች ያላቸው የድርጅቱ መሪዎች ተከፋፍለው ከእስር ቢወጡ በትግሉ ላይ ሊያደርስ የሚችለው አደጋ ስጋት አሳደረብን። አውስትራሊያ ሰማይ ላይ ተጽፎ ፐርዝ ከሚባለው ከተማ ወደሃገር ቤት የተላከው ደብዳቤ መሪዎቻችን በአንድነት አስር አንደገቡ በአንድነት የመውጣትን አስፈላጊነት በአጽንኦት የጠየቀ፣ በተለይ በህግና በሞራል አኳያ ጥያቄ ላነሱት ሃይሎች ምላሽ የሚሆኑ ነጥቦችን ያካተተ ነበር። እኛ ከእስር ውጭ ያለነው ወገኖቻቸው ከእስር ቤት ውጭ ያለውን እውነታ በተቻለ መጠን በመግለጽ ጉዳዩ ሊያሳስባቸው እንደማይገባ የሚያስረዳ ነበር። በተለይ የህዝብን አስታየየት በሚመለከት ለነበራቸው ስጋት ወያኔን ማንም ስለማያምነው ህዝብ መፈታታችሁ አንጂ ለመፈታት የደረሳችሁበት ስምምነት አያሳስበውም። በእዚህ ስምምነት መሰረት የፕሮፖጋንዳ ስራ እሰራለሁ ብሎ ወያኔ ቢነሳ የበለጠ ኪሳራ የሚደርስበት እርሱ አንደሚሆን፣ ለቅንጅት መሪዎች ህዝብ ያለው አመኔታ ወደር የሌለው መሆኑን የሚያስረዳ ነበር። የቅንጅት መሪዎች ከመፈታታቸው በፊት የተደረገውን ስምምነት በመጣስ ወያኔ ቀንና ማታ ያካሄደው ፕሮፓጋንዳ የበለጠ ኪሳራ ውስጥ አንደጣለው አይተናል። ህዝብ ለቅንጅት መሪዎች ያለውን ከበሬታ፣ በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ ከመቼውም፣ በላቀ ደረጃ ገለጸ አንጂ የቀነሰባቸው ነገር አልተገኘም። እዚህ ላይ አንድ አንድ የፖለቲካ ድርጅቶች ይህንን የመፈቻ ሰነድ ሰበብ በማድረግ በቅንጀት ላይ ጥቃት ሊሰነዝሩ አንደሚችሉም ደብዳቤው ገልጧል። ያሰብነው አልቀረም ጥቂት የኢህአፓ አመራርና ጉደኛው ልደቱ አያሌው ይህን ሲያደርጉ ተስተውሏል። በሌላ በኩልም በተለይ ህግን አስመልክቶ የቀረበው መከራከሪያ ስለ ህግ መጨነቅ በህግና በስርአት የሚመራ መንግስት ባለበት ሃገር መሆኑን፣ ወያኔ ለመግደል ለማሰር ማስረጃ እንደማይፈለግ ሁሉ የተወሰነ ሰነድ በመፈረም ማስረጃ መስጠት ነው የሚል ክርክር እርባና የሌለው መሆኑን የሚሳይ ነበር። ለሁለት አመት ለእስር ሲዳረጉ አንዴ የሞት ፍርድ ቀጥሎም እድሜ ልክ እስራት ይፈረድባቸው በማለት የወያኔ ፍርድ ቤት ትእይንት ሲሳይ የሚውለው፣ ተፈጸመ ለተባሉት ወንጀሎች ብጣሽ ማስረጃ ይዞ ነወይ የሚል ጥያቄ ያነሳ ነበር። ደብዳቤው እንደሚለው መሪዎቻችን በመጨረሻ ፈርመው የወጡትን ሰነድ ፈርመው ቢወጡ፣ በህግ በሞራል፣ በፖለቲካ፣ በህዝብ ግንኙነት ሊያስከትል የሚችላቸውን አዎንታዊና አሉታዊ መዘዞች የዘረዘረ እራሱን የቻለ ታሪካዊ ሰነድ ነው። ወደፊት ሰነዱን በሙሉ ማቅረብ የሚቻልበት ግዜ ይመጣ ይሆናል።

በመነፈጋቸው፣ ወከባ ስለበዛባቸው የተከሰቱ ናቸው" በማለት፣ እንዲሁም ሃዘኔታንና ሌሎችንም ምክንያቶች እየደረደርን ደንዝዘን ተቀመጥን፡፡

ውሎ አድሮ ችግሩ ይህ እንዳልሆነ መረዳት ጀመርን፡፡ ሆኖም ግን ግልጽ የሆኑ የጥፋተኛነት መረጃዎች በእጃችን ቢኖሩም ወገን ሳንለይ መሪዎቻችን አንድነታቸውን አጥብቀው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ሞክረናል፡፡ ከግል ስማቸው፣ ክብራቸው፣ ስሜታቸውና ፍላጎታቸው በላይ ለሆኑት የህዝብና የሃገር ጉዳይ ቅድሚያ ሰጥተው በአንድ እንዲቆሙ፣ ትልቅ ተስፋ የጣለባቸውን ህዝብ እንዳያስቀይሙ፣ በእነሱ አመራር ተማምኖ ውድ ህይወቱን ጉልበቱን ገንዘቡን ግዜውን እውቀቱን በከፍተኛ ደረጃ መስዋእት ያደረገውን በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ የሚገኘውን በርካታ ኢትዮጵያዊ አስበው እጅ ለእጅ ተያይዘው እንዲጓዙ ብዙ ጥረት ተደርጓል፡፡ አንዳንዴ ይህ አቋም መጥፎና ጥሩውን መለየት የምንችልበት የሞራል መነጽር የሌለን፣ ውሳኔ ወስነን የውሳኔያችንን መዘዝ ለመቀበል ወኔ የሌለን መሃል ሰፋሪዎች እስከሚያስመስለንና ለትዝብት እስከሚዳርገን፣ እባካችሁ ለሃገርና ለወገን ስትሉ በአንድነት ተንቀሳቀሱ ብለን ሁሉንም ተማጽነናል፡፡

ድርጅታችን ቅንጅት በአመራሩ ይሁን በአባለቱ መሃከል የሚነሱ ችግሮችን መፍታት የሚችልበት ዴሞክራሲያዊ ህገ-ደንብ፣ ስርአትና መዋቅር የሌለው፣ በግለሰቦች መልካም ፈቃድ ተገጣጥሞ የቆመ አልባሌ የግለሰቦች ስብስብ እስከሚመስል የድርጅታችን መሪዎች በአንድነት እንዲሰሩ ለማድርግ በሃገራችን የፖለቲካ ታሪክ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን የልመና፣ የምልጃ፣ የተማጽኖና የሽምግልና ስራ ተሰርቷል፡፡ የእዚህን ዝረዝር ለታሪክ ጸሃፊዎች መተው ይሻላል፡፡ አልሆነም፡፡

ልመናው፣ ምልጃው መማጠኑ ቅንጅትን ስራ እንደይሰራ ሽባ አደርጎት አቆየው፡፡ እያደርና እየዋለ ልመናውና ምልጃው አንድ አንዶቹን የድርጅቱን መሪዎች የድርጅቱን ህልውና ጭምር የሚፈታተኑ እርምጃዎች መወሰድ እንዲጀምሩ አደፋፈራቸው፡፡ ከሁሉም የሚያሳዝነው በእዚህ ውዝግብ ውስጥ ዋናውን አፍራሽ ሚና የሚጫወቱት የድርጅቱ ሊቀመንበር ሆነው አረፉት፡፡ ሊቀመንበሩን በእዚህ በተሳሳተ መንገድ የሚገፏቸው፣ በቂ መረጃ እንዳያገኙ አፍነው የያዟቸው ግለሰቦች ናቸው ተባለ፡፡ ይህም እውነት ሳይሆን አይቀርም በሚል ጥርጣሬ ሊቀመንበራችን የተመጣጠነ ሚዛናዊ መረጃ አግኝተው የመሪነት ሀላፊነታቸውን በሚገባ እንዲወጡ ለማድረግ ያደረግነው ጥረት የትም ሳይደርስ ቀረ፡፡ የድርጅቱ ሊቀመንበር፣ የአንድነት፣ የዴሞክራሲያዊነት፣ የህግና የደንብ አክባሪነት፣ የትእግስትና የመቻቻል አርአያ ሆነው ከማንም በላይ ልቀው መገኘት ሲገባቸው ድርጊታቸው ሁሉ ከእዚህ ተጻራሪ ሆነ፡፡ መሪዎቻችን ከእስር ከተፈቱ በኋላ በድርጅታችን ሊቀመንበር ሲወሰዱ የነበሩ ድርጅታዊ ስርአትንና ደንብ ያልተከተሉ አነስተኛ ናቸው ተብለው ሲታለፉ የነበሩ ድርጊቶች ውለው አድረው የድርጅቱን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ፣ መሰረታዊ የሆኑትን የድርጅቱን ዴሞክራሲያዊ ምንነት የሚፈታተኑ ሆነው አረፉት፡፡

"በድርጅቱ ውስጥ ከፍተኛ ሀላፊነትና ብቃት ያላቸውን ግለሰቦች ከድርጅቱ አግጃለሁ፡፡ የድርጅቱን ሊቀመንበርነት ቦታ ከድርጅቱ ደንብና ስርአት ውጭ በውክልና ለፈለግሁት ግለሰብ ሰጥቻለሁ" የሚል ውሳኔ ሊቀመንበሩ አስተላለፉ፡፡ ከእዚህ ውጭ ቅንጅትን ከሚያክል ትልቅ ራእይ ካለውና ተስፋ ከተጣለበት ድርጅት የማይጠበቅ፣ የድርጅቱን

አባላትና ደጋፊዎቸ በሃፍረት የሚያሸማቅቅ፣ ቅንጅትን በወያኔና የቅንጅትን በጎ በማይመኙ ድርጅቶችና ግለሰቦች አይን መሳለቂያ የሚያደርግ፣ በድርጅት የዲሲፕሊንና የስነስረአት ደንብ መሰረት በጥብቅ ሊያስጠይቅ የሚችል፣ ጨዋነትና ስልጡንነት የጎደለው አይን ያወጣ ሃሰት፣ አሉባልታና ተራ ወሬ የተሞላው ዘመቻ የቅንጅትን መሰረታዊ የፖለቲካ ራእይና እሴቶች ተሸክመው በሚንቀሳቀሱ የድርጅቱ አመራሮች ላይ ተከፈተ። ይህ ዘመቻ የተካሄደው መሪዎቻችን በእስር በሚማቅቁበት ወቅት በቅንጅት ላይ ከፍተኛ ጥቃት ሲነዘሩና በእዚህም የተነሳ በውጭ በሚገኘው ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ውስጥ አድማጭ አጥተው በነበሩ አንድ አንድ የውጭ የመገናኛ አውታሮች መሆኑ ብዙን የቅንጅት ደጋፊ አቆሰለው።

ሊቀመንበሩ በተገኙበት የዋሽንግተን ዲሲ ስብሰባ ላይ ከተፈጸመው አሳፋሪ ድርጊት ሳናገግም፣ በቅርቡ በሚነሶታ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች በተሰባሰቡበትና ሊቀመንበሩ በተገኙበት መድረክ፤ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎችን አንገት የሚያስደፋ፣ ቅንጅትን ለከፍተኛ አደጋ የሚያጋልጥ ወያኔን መማለጃ የሚመስል ንግግር በአቶ በድሩ ሲነገር አደመጥን። በየመድረኩ ዋናው ትግል ከወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝ ላይ መሆኑ ቀርቶ በአንድ ላይ በመወሰንና በአንድ ላይ በመታሰር አበሳቸውን ያዩትን የቅንጅት መሪዎች ስም ማጥፋትና መጥላላት ሆኖ አረፈው። ቀኑ መሽቶ ሲነጋ ውሸት መሆኑ በቀላሉ ሊረጋገጥ የሚችል ተራ ወሬ ማናፈስ ትልቁ የፖለቲካ ስራ ሆነ። የቅንጅት አመራር በጋራ የወሰነውን የሰላማዊ ህዝባዊ እምቢተኛነት ውሳኔና ህዝብም ምለሹን በመስጠት የሞተለትን ጥሪ ሳይቀር "ከቅንጅት ሊቀመንበርና ከአብዛኛው አመራር እውቅና ውጭ ጥቂት ዘረኛ የሆኑ ግለሰቦች የፈጸሙት ነው" ተባለ። በእነዚህ መድረኮች የሚነገረውን አሳፋሪ ንግግር ያደመጠን፣ ቅንጅትን እንደ ድርጅት "የዴሞክራሲያዊና የሰለጠነ ፖለቲካ ተምሳሌ ነው" በማለት ድጋፌችንን የሰጠንና ሌሎችም እንዲደግፉት የተማጸንን በሙሉ "ይህ ድርጅት በሆዱ ስንት ጉድ ይዞ ነበር" የሚል ጥያቄ እንድናነሳ አድርጎናል።

ይህ ሁሉ በአንድ ላይ ተደምሮ፣ ቅንጅትን ከራእዩ በመነሳት የደገፍነው በመሉ፣ በተለይ ደግሞ በከፍተኛ ጨዋነት፣ ትእግስትና አርቆ አስተዋይነት እስካሁን በድርጅቱ ውስጥ የተከሰተውን ቀውስ ለማስተናገድ እልህ አስጨራሽ ፈተና የተፈተነውን የቅንጅት አመራር ጨምሮ፣ መሰረታዊ ጥያቄ ማንሳት ከሚገባን ደረጃ አድርሶናል የሚል እምነት አለኝ።

ለአንድነትና ለመቻቻል ተብሎ እሰካሁን ብዙ ግዜ ጠፍቷል። የጠፋው ግዜ ትክክልም ተገቢ ነበር። ህዝብ ለቅንጅት አንድነት ለሚሰጠው ትልቅ ቦታ ሲባል፣ የተፈጠረውን ችግር በድርጅቱ ህገ ደንብ መሰረት በጥድፊያ መፍትሄ ሰጥቶ ለመንቀሳቀስ አለመፈለጉም ለህዝብ ስሜትና ፍላጎት የቅንጅት አመራር ትልቅ ቦታ እንደሚሰጥ የሚያረጋግጥ ነው። ይህም በጎ ነው። ችግሩ የቅንጅት አመራር ቀናነትና በጎ ፍላጎት ማጣት ሳይሆን እስካሁን ለማናችንም ግልጽ ባልሆነ ምክንያት፣ ከጥርጣሬ በስተቀር፣ ሊቀመንበሩና ጥቂት ግለሰቦች የድርጅቱን ህገ- ደንብ አክብረው በአንድነት በድርጅቱ ውስጥ በአባለቱ የተሰጣቸውን ሃላፊነት በአግባቡ ለመንቀሳቀስ ፈጽሞ ፍላጎቱ የሌላችው መሆኑ ነው።

ዞሮ ዞሮ ጥያቄያችን "ቅንጅት የተቋቋመው የኢትዮጵያን ህዝብ የመብቱ ባለቤት ለማድረግ በመሆኑ፣ ይህን ሃለፊነቱን በሚገባ ለመወጣት እንዳይችል ተብትቦ በያዘው

የውስጥ ቀውስ እንደታሰረ አስከመቼ ይቀጥላል?" የሚለው ነው። ችግሩ ባይከሰት ሁላችንም ደስ ባለን ነበር። ይህን ችግር ለመፍታት ከሚገባው በላይ ጥረት አድርገናል። ጥረቱ ምንም ውጤት እንደማያመጣ ግልጽ በሆነበት ወቅት፣ ለችግሩ እልባት ሰጥቶ መንቀሳቀስ ከአንድ ድርጅት የሚጠበቅ አይደለምን? ይህንን አለማድረግ ሃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ብቃትና ድፍረት ማጣት አያስመስልምን? ቅንጅትን ለባሰና ለከፍተኛ ጉዳት የሚያጋልጥ አይሆንምን?

በእዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰጥ መፍትሄ የቅንጅትን እሴቶችና ራእዮች የድርጅቱን ዴሞክራሲያዊ ህገ ደንብና ስርአት የተከተለ፣ ስልጡንነትና ጨዋነት የተላበሰ፣ የዴሞክራሲ ሃሁ ሳያውቁ በዴሞክራሲ ስም ለሚምሉና ለሚገዘቱ የፖለቲካ ድርጅቶችና ግለሰቦች ማሳሰቢያና ለህብረተሳባችን የዘለቄታ ትምህርት የሚሰጥ መሆን አለበት።

መወሰድ ስለሚገባው እርምጃ ስናነሳ በቅድሚያ ግልጽ መደረግ ያለበት ጉዳይ አለ። ዛሬ ቅንጅት ባስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት የሚችልበት ሁኔታ ላይ አይደለም። ጠቅላላ ጉባኤ ለመጥራት የጠቅላላ ጉባኤ አባለት መምረጥ የሚቻሉባቸው የቅንጅት ወረዳ የፓርቲው መዋቅሮች መኖር ይገባቸዋል። በወረዳ ደረጃ ቀድሞዎቹን የቅንጅት አባል ድርጅቶች አባላት ያዋሃደ፣ በተለይ በምርጫው ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች የቀድሞ የቅንጅት አባል ድርጅቶች አባል ሳይሆን፣ የተዋሃደው ቅንጅት አባል ለመሆን ቆርጠው የነበሩትን በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ አባላትን በየወረዳው መመልመልና ማደራጃት ያስፈልጋል። የቅድመ-ቅንጅት ድርጅቶችን መሳሳብ የሚያስቆመው በቅንጅትነት የሚመዘገበው አዲስ አባል ነውና ይህ ትኩረት ሊሰጠው የሚጋባ ጉዳይ ነው። ይህ ስራ ተጠናቆ የቆዩና አዲስ አባላት በአንድነት የተደራጁበት የወረዳ መዋቅር ሊኖር ይገባዋል። በተወሰነ ግዜ ውስጥ የቅንጅትን አደረጃጀት፣ አሰራር፣ እሴቶቹና መርሆዎቹን በሚመለከት ለአባላት ስልጠና መሰጠት አለበት። የቀድሞ ድርጅታዊ አባልነት መሳሳብ እንዳይኖር፣ አበላት በአካልም በመንፈስም ቅንጅታዊ የሆነ አመለካከትና አሰራር እንዲኖራቸው የቅንጅት ዋናው ጽ/ቤት በሚያጣው እቅድ መሰረት የማደራጀትና የማስተማር ስራ መሰራት አለበት። የአባልነት መብት አግኝተው የተመዘገቡ የፓርቲው አባላት ተሰብስበው በፓርቲው ህግና ደንብ መሰረት ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የሚገኙ ተወካዮችን መምረጥ ይኖርባቸዋል። ቅንጅት ህጋዊ ባልሆነበት፣ ስሙን ለወያኔ ላደሩ የወያኔ አገልጋዮች በትእዛዝ እንዲሰጥ በተደረገበት፣ ቢሮ መክፈትና ስብሰባ መጥራት እንዳይችል ወከባና ማስፈራረት በሚደረጉበት በዚህ ወቅት የድርጅቱ ከፍተኛ የስልጣን ባለቤት የሆነውን ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት አይቻልም። ስለዚህም በድርጅቱ ውስጥ የተከሰተውን ችግር እልባት ለመስጠት ጠቅላላ ጉባኤ እስኪሚጠራ ድረስ እናንጠልጥለው የሚል ሃሳብ ትርጉም የለውም። በሊቀመንበሩ የሚመራው ቡድን እስካሁን በድርጅቱ ላይ ያካሄደው ጉዳት ቀላል አይደለም። እንዲህ አይነቱን ጉዳት እያካሄደ እንዲቀጥል ግን ግዜ ሊሰጠው የሚገባ አይደለም።

ከጠቅላላ ጉባኤ በታች የሚገኘው ሌላው ከፍተኛ አካል የላእላይ ምክር ቤቱ ነው። የላእላይ ምክር ቤቱም ቢሆን ኮረም ሞልቶ ውሳኔ መወሰን እንደማይችል በተደጋጋሚ በተጠራ ስብሳበ ማረጋገጥ ተችሏል። በተገኙት የላእላይ ኮሚቴ አበላት መገልገል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሆኗል። ከላእላይ ምክር ቤቱ ቀጥሎ ከፍተኛው ስልጣን ያለው በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው እጅ ነው። በመሆኑም አሁን ቅንጅት በሚገኝበት ሁኔታ

የቅንጅትን የየቀኑን ስራዎች መስራት ብቻ ሳይሆን መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎች የመስጠት ሃላፊነት የተጫነው በእዚህ አካል ላይ ነው። የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በአካባቢው ከሚያገኛቸው የምክር ቤት አባላት ጋር መምከር በሚገባው ጉዳዮች ላይ እየመከረ ውሳኔዎችን እየወሰነ ድርጅቱን ወደፊት መውሰድ ይገባዋል። የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ከሌሎች ስራዎቹ ጎን ለጎን በአፋጣኝ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የድርጅቱን ሊቀመንበርና ጥቂት የምክርቤቱ አበላት ከድርጅቱ ህገ ደንበ ውጭ ድርጅቱን የሚጎዳ እንቅስቃሴቸውን እንዲያቆሙ ማድረግ ነው። በእዚህ ጉዳይ ላይ የድርጅቱ ህገ ደንብ በሚያዘውና ከእዚህ ቀደም በልደቱና በጓደኞቹ ላይ የተወሰደውን አይነት እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል። ማንንም ግለሰብ ከድርጅቱ በላይ እንዳልሆነ፣ የድርጅቱ ህገ-ደንብ  ከድርጅቱ ሊቀመንበር አንስቶ አስከተራው አባል በእኩልነት እንደሚሰራ በእዚህ ህግ ፊት ሁሉም እኩል መሆናቸውን የሚያሳይ እርምጃ በመውሰድ ለችግሩ እልባት መስጠት ያስፈልጋል። በመሆኑም

- የደርጅቱን ህገ-ደንብ በማያከብሩት፣ ድርጅቱን የሚጎዳ እንቅስቃሴያቸውን ባላቆሙት በሊቀመንበሩና ከእራሳቸው ጋር በተባበሩት ግለሰቦች ላይ፣ ጉዳያቸው በደርጅቱ ህገ-ደንብ መሰረት ተጣርቶ፣ ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች ምላሻቸውን ሰጥተው ውሳኔ እስከሚያገኙ ድረስ ከአመራር ሃላፊነታቸው የታገዱ መሆኑን ግልጽ መደረግ ይኖርበታል። እነዚህ ግለሰቦች ይዘውት የነበርው የስራ ሃላፊነት በህገ ደንቡ መሰረትና  በጊዚያዊነት ተተኪዎቻቸው ተረክበው ስራቸውን መቀጠል ይኖርባቸዋል።
- በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ የሚገኙት የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ዋናው ትግል በሃገራችን የሰፈነውን አምባገነናዊ የፖለቲካ ስርአት መቀየር መሆኑን በመረዳት፣ ትኩረታችንን የቅንጅት ስራ አስፈጻሚ በሚያጣው የስራ እቅድ ላይ እንድናደርግ መመሪያ መስጠት ያስፈልጋል።
- አባላትና ደጋፊዎች በማንኛውም ወቅትና ግዜ በመሃከላቸውም ይሁን ከሌሎች የፖለቲካ ቡድኖች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት፣ እስካሁን እንዳደረጉት፣ እራሳቸውን ቅንጅትን ከመሰለ ዴሞክራሲያዊ የሆነ ድርጅት በሚጠበቅ ጨዋነትና ስልጡንነት እያስገዙ እንዲንቀሳቀሱ፣ በተለይ በሃገር ውስጥና በውጭ ከተራ ስነምግባርና ጨዋነት በወጣ መንገድ በመጓዝ፣ ትግሉን ከአምባገነኑ ወያኔ/ኢህአዴግ ጋር ሳይሆን ከቅንጅት ጋር ያደረገውን የሊቀመንበሩን ቡድን ትንኮሳ በሰለጠነ መንገድ እንዲያስተናግዱ ማድረግ ይገባል።
- በድርጅቱ ውስጥ የተነሳውን ቀውስ በተራ አሉባልታና ወሬ ዙሪያ ለማሽከርከር የሚደረገውን ሙከራ፣ ቅንጅትን የገጠመውን መሰረታዊ የሆኑ የፖለቲካ ችግሮችና መፍትሄያቸውን በሚሻ አጀንዳና ውይይት እንዲተካ ማድረግ፣ ከሊቀመንበሩና ከደጋፊዎቻቸው ጋር ያለው ልዩነት በጥቅሉ ዴሞክራሲን በተለይ ድግሞ ፓርቲ ዴሞክራሲንና ህገ-ደንብ የተመለከተ መሆኑን ለደጋፊዎችና ለአባላት ሳይታክቱ ማስረዳት ይገባል።
- ሊቀመንበሩና ደጋፊዎቻቸው በአደባባይ ለመናገር ያልደፈሩትና በቅንጅት ህገ ደንብ መፍትሄ ማግኘት አይችልም ብለው የሚያስቡት መሰረታዊ ልዩነት ካላቸው፣ ቅንጅትን ለቀው በፈለጉት መንገድ መንቀሳቀስ መብታቸው መሆኑንና ወደፊትም ቢሆን እንዲህ አይነቱ ሁኔታ በቅንጅት ውስጥ ሲከሰት፣ መለያየትን ከመጠፋፋት ጋር ሳያይዙ በጋራ ሊያሰሩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ በመገኛኘት ለመስራት የሚቻል መሆኑን ግልጽ ማድረግ ይገባል። ገና ለገና "ሁለት ቡድኖች

ከተፈጠሩ ከህዝብ የሚገኝ ሁለንተናዊ ድጋፍ ይከፈላል፤ ወይም ሌላው እስካለ በቂ ድጋፍ አላገኝም" በሚል ብሂል ጭፍን የማፍረስ ተግባር ላይ መሰማራት በሃገራችን የፖለቲካ ታሪክ ያስከተለውን ጉዳት በማስረዳት ደጋፊዎች ይሁኑ ባላንጣዎች ሁሉን አውዳሚ ከሆነ ተግባር እንዲርቁ መታግል ይገባል። በእዚህ መሰረት ማንኛውንም አይነት አመለካከት የተሸከመ ድርጅት፣ ግለሰቦችን በሃገራችን ማንገስና ንጉሳዊ ስርአት መመለስ አለብኝ ብሎ የሚያስበው ሳይቀር፣ ጉዳዩን ለህዝብ አቅርቦ በህዝብ ድምጽ ለመዳኘት እስከፈቀደ ድረስ፣ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ድምጹን ለሚሰጥበትና ድምጹ ለሚከበርበት የፖለቲካ ሁኔታ መፈጠር በጋራ ለመታገል እንደሚቻል ማስረዳት ያስፈልጋል። "በየትኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ ላይ፣ በየትኛውም የፖለቲካ ሰውና አመለካከት ላይ ፍርድ መፍረድ የሚገባው ህዝብ ነው" ብሎ ቅንጅት እንደሚያምንና ለእዚህ አይነቱ ፍርድ እራሳቸውን ለማቅረብ ፈቃደኛ የሆኑ ሁሉ የዴሞክራሲያዊ ትግሉ አካል አድርጎ እንደሚያያቸው ግልጽ ማድረግ ይገባል። ባለንበት ወቅት ቅንጅት የማይስማማው "ከህዝብ ፈቃድ ውጭ ስልጣን ላይ መውጣት" አለብኝ ከሚል አካል ብቻ እንጂ ከየትኛውም ድርጅት አመሰራረት፣ አሰራርና ፖሊሲዎች ጋር አይደለም።

## *2- ቅንጅትን ለማጥፋትና ለማዳከም በስልጣን ላይ ካለው አገዛዝ የሚሰዘርበትን ጥቃት በሚመለከት።*

ወያኔ/ኢህአዴግ ያለህዝብ ይሁንታ ከያዘው ህገ-ወጥ የመንግስት ስልጣን ይነቅለኛል ብሎ የሚፈራው ቅንጀትን ነው። በመሆኑም በስልጣን ላይ ለመሰንበት ቅንጅትን ማጥፋት ወይም ማዳከም የሚል ፖሊሲ ነድፎ መንቀሳቀስ ከጀመረ ሰንብቷል። ግድያው እስራቱ ማፈናቀሉ፣ ማሳደዱ፣ ማስፈራራቱ፣ ገንዘብ መበተኑና መደለሉ የእዚሁ ቅንጅትን የማጥፋቱ መርሃ ግብር አካል ናቸው። አሁን ድግሞ የወያኔ ባለስልጣናት እንደቤት ሰራተኞቻቸው በሚያዟቸው ግለሰቦች የተሞሉትን የፍርድና የምርጫ ቦርድ ተቋማት በመጠቀም፣ የቅንጀትን ስምና አርማ የወያኔን ፍላጎት ለማስፈጸም ላቋቋሟቸው ተለጣፊዎች እንዲሰጡ አድርገዋል። ቅንጅት በሚል ስም ተወዳድሮ የግንቦት 1997 ምርጫ ያሸነፈውን የድርጅት ስም ለማይመለከታቸው ቡድኖች ወያኔ የሚያከፋፍለው ቅንጅት በሚል ስም ከእስር የተፈቱት የቅንጅት አመራሮች እንዳይንቀሳቀሱ ለማድረግ በማሰብ ነው። ህጋዊነት የላችሁም በሚል ሰበብ ቅንጅት በስሙ የስብሰባ አዳራሽና ቢሮ እንዳይከራይ፣ አባላቱንና ደጋፊዎቹን ለስብሰባ እንዳይጠራ ለማድረግ ታስቦ የተፈጸመ ድርጊት ነው። የወያኔ አላማ፣ ቅንጀት ስሙን ለማስመለስ ወያኔ እንደፈለገ ትእዛዝ በሚሰጠው ፍርድ ቤት ጊዜውን እንዲያጠፋና በእዚህም ሰበብ ድርጅቱ እራሱን የማዋቀር፣ ቢሮዎች የመክፈት፣ አባላቱን የማሰባሰብ ስራ ሳይሰራ የቅርቡም ይሁን የሩቁ 2010 ምርጫ ለማካሄድ ነው። የወያኔ አለማ ይህ ከሆነ የቅንጀት ምላሽ ምንድን መሆን ይገባዋል?

በቅድሚያ "ሀገርና አለም ያወቀውን ስም፣ ወያኔ ይሉኝታ አልባና አምባገነናዊ በሆነ መንገድ ሂዶ ከህጋዊ ባለቤቶቹ ከነጠቀ፣ በሃገሪቱ ውስጥ ከወያኔ ፍላጎት ውጭ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶች ለማየት ይፈልጋል ወይ?" የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ ነው:: የእዚህ ጥያቄ መልስ አይፈለግም ነው። ወያኔ በግንቦት 97 ምርጫ በሚገባ የቀሰመው ትምህርት ቢኖር ዴሞክራሲያዊ በሆነ ውድድር ቅንጅትን የመሰለ ጠንካራ ተቃዋሚ በቀላሉ ከስልጣኑ ሊነቅለው እንደሚችል ነው። ይህ በመሆኑም አንዳንድ

የቅንጅት አመራር እንደጠቆሙት "የስሙን ችግር ለማቃለል በሌላ ስም መንቀሳቀስ ይሻላል። ህዝብ ከቅንጀት ራእይ እንጂ ከስሙ ጋር አይደለም የተሳሰረው" የሚሉት ሃሳብ ትርጉም አይኖረውም።

የወያኔ ችግር ቅንጀት ከሚለው ስም ጋር ሳይሆን ጠንካራ ተቃዋሚ ለማየት ከላመፈለግ ጋር መሆኑን በመረዳት የተከሰተውን ችግር ስም በመቀየር ሳይሆን የችግሩን ምንጭ ከስሩ ለማድረቅ ቅንጀት ቆርጦ መነሳት ይኖርበታል። ይህ ችግር በሃገራችን ነጻ ፍርድቤትና ነጻ የምርጫ ቦርድ ካለመኖራቸው ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ችግር የገዛ ህገ-መንግስቱን እንዳሻው የሚጥስ መንግስት በሃገር ላይ በመንገሱ የመጣ ችግር ነው። ቅንጅት የሚለውን ስም በሌላ ስም ቀይሮ፣ ሌላ ወያኔን የሚታገል ጠንካራ ድርጅት መገንባት ይቻላል ብሎ ማሰብ "ሰጎን አንገቷን አሸዋ ውስጥ ቀብራ ሁለንተኛዬን ደብቂያለሁ" ብላ እራሷን ካታለለችብት ሁኔታ ልዩነት አይኖረውም። ወያኔ ህገ-መንግስቱን በጣሰ ቁጥር፣ እንዳሻው የሚያዝባቸውን ተቋማት በመጠቀም ህገ-ወጥ ተግባራት ባከናወነ ቁጥር፣ ዋሽቶና ቀላመዶ አንዴ እርቅ አንዴ ወይይት ባለ ቁጥር፣ የቅንጅት አመራር ማለቂያ የሌለው "የማርያም" መንገድ ለወያኔ በመልቀቅ መቀጠል አይችልም። እስካሁን ከፈጸማቸው ሽፍጦች ተነስተን የወያኔን ምንንነት ካልተረዳን ህዝብንና እራሳችንንም ለከፍተኛ መከራ የምናጋልጠው ይሆናል።

ከምርጫው በፊትና ከምርጫው በኂላ የታየውን በሽፍጥ የተሞላውን የወያኔ ባለስልጣናት ባህርይ በቅጡ ባለመረዳት የቅንጅት አመራር የወሰናቸውን አንዳንድ ውሳኔዎች ወደኂላ ተመልሶ ማጤን ይገባዋል። የቅንጅትን ስም በሚመለከት ወያኔ እንደለመደው፣ ለአለም አቀፍ ማህበረሰቡንም ሆነ ለሃገር ሽማግሌዎች ጉዳዩ በፍርድቤት የተወሰነ ስለሆነ ህጉን ተከትለው በሌላ ስም መንቀሳቀስ ይችላሉ የሚል ምላሽ መስጠቱ አይቀርም። ይህ ምላሽ "የቤት ውስጥ መቀመጥ አድማ ያንሱልኛና ከጸሃይ በታች ባሉ ጉዳዮች ላይ እደራደራለሁ" ብሎ በመዋሸት በአለም አቀፍ ማህበረሰብ አማካይነት ወያኔ ከላከው ምለጃና በማግስቱ ከፈጸመው ነውረኛ ድርጊት ጋር መመሳክር አለበት። እንደገናም ከእስር ቤት ለመውጣት የቅንጀት መሪዎች በሃገር ሽመግሌዎች አማካይነት የተደረሰበትን የድርድርና ውይይት ስምምነት በመጣስ፣ እስረኞቹ ከእስር ከመፈታታቸው ጀምሮና ከተፈቱም በኂላ የተፈጸመውን ሀፍረተ-ቢስ ድርጊት ሁሉ ልብ ማለት ይጠይቃል።

የቅንጅት ስም ተራ ስም አይደለም። ይህን የምለው በእዚህ ስም አማካይነት ተሰልፈው የወደቁ ሰማእታት መኖራቸውን በመጥቀስ ስሜታዊ ክርክር ለማድረግ አይደለም። ይህንን ስም በሚመለከት ወያኔ የወሰዳቸውና እየወሰደ ያለው እርምጃዎች የወያኔን መሰረታዊ ባህሪ የሚያንጸባርቁ ናቸው። የስሙ ጉዳይ "በሃገራችን ከወያኔ ፈቃድና ፍላጎት ውጭ የሚንቀሳቀሱ ጠንካራ ስላማዊና ህጋዊ ፓርቲዎች እንዲኖሩ ወያኔ ፍላጎት አለው ወይንስ የለውም?" የሚለው ጥያቄ የሚሽከረከርበት አብይ ጉዳይ ነው። እውን ነው የቅንጅት አመራር በእዚህ ስም ዙሪያ የሚያደርገውን ትግል ወደ ፍርድ ቤትና ወደ ምርጫ ቦርድ መውሰድ አይችልም። አዎን በእዚህ ስም ዙሪያ ህዝባዊ አምቢተኛነትን መሰረት ያደረገ ትግል ለማድረግ ሃገራዊ ሁኔታው አያመችም። ቅንጅት ድርጃታዊ መዋቅሩን አልዘረጋም። አባለቱን አላሰባሰበም። መፍትሄው ምንድነው?

መፍትሄው ቅንጅት ሰላማዊና ህጋዊ እንቅስቀሴ ለማድረግ የተቋቋመ፣ በየግዜው በሚደረግ ምርጫ ተወዳድሮ ስልጣን ለመያዝ የሚታግል ድርጅት መሆኑን፣ ይህንን ለማድረግ ይህ ድርጅት ህገወጥ በሆነ መንገድ የተወሰደበትን ስሙ እንዲመለስለት፣ በህጋዊነት በሃገሪቱ በመንቀሳቀስና አባላቱን ማሰባሰብ ቢሮዎቹን መክፈት እንዲችል ባፋጣን ምላሽ እንዲያገኝ ማድረግ ነው። ይህንን ለማድረግ ዛሬ ቅንጅት ከሚለው ስም ጋር፣ ነገ ደግሞ ከሌሎች ጉዳዮች ጋር እየተሳሰረ የሚገጥመው ችግር ቅንጅት ፓርላማ ላለመግባት ከስጣቸው ምክንያቶች ጋር በጥብቅ የተሳሰረ፣ መፍትሄውም ቅንጅት ፓርላማ ለመግባት መሟላት አለባቸው በማለት ካስቀመጣቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ጋር የተቆራኘ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ለማስታወስ ያኽል።

"ከወያኔ ፓርቲ ነጻ የሆነ የፍትህ ስርአት፣ የሚድያ አገልግሎት፣ የምርጫ ቦርድ፣ የመከላከያ የደህንነትና የፖሊስ ሃይል የለም። በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ሃገራዊ ዴሞክራሲም ሆነ የፓርላማ ዴሞክራሲ መገንባት አይቻልም። ይህንን ለማስተካከል ወያኔ ፈቃደኛ እስከሆነ ድረስ የህዝብንም ድምጽ እንደሰረቀ እያወቅን ለሚቀጥሉት አምስት አመታት በስልጣን ይቀጥል። ዋናው አላማችን በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመግባት እንጂ ሰልጣን ላይ ለመንጠላጠል አይደለም። በእዚህ ጉዳይ ላይ ውይይት እንጀምር" በማለት ነበር ቅንጅት ጥያቄውን ለወያኔ ያቀረበው። የወያኔ ምላሽ፣ "አይሆንም ደግሞ አንተ ማነህና? የምን ድርድር" በመሆኑ የቅንጅት አመራር ፓርላማ ላለመግባት ወስኖ፣ ሕዝቡንም ለእነዚህ መሰራታዊ የዴሞክራሲ ዋስትና ለሆኑት ተቋማት ምስረታ ትግል እንዲያደርግ ጥሪ አድርጎ፣ በመጨረሻም ህዝብም በህይወቱ መስዋእትንት ሲከፍል፣ መሪዎቹም ለእስር ተዳረጉ።

የቅንጅት አመራር ስለነጻ ተቋማት ጥያቄ ካነሳበት ወቅት ጀምሮ በሃገራችን የታየው ሁኔታ እውነትም እነዚህ ተቋማት ምንም አይነት ነጻ ህልውና የሌላቸው በወያኔ በጎ ፈቃድ የሚተነፍሱ መሆናቸውን ነው። የህዝብ መብትና ነጻነት ማስከበሪያ ሳይሆኑ የወያኔ የአፈና መዋቅር ተጨማሪ ክንዶች መሆናቸው ታይቷል። ሩቅ ሳይሄድ የቅንጅት መሪዎች በተከሰሱበት ፍርድ ቤት የታየውን የፍትህ ቧልት በታሪካችን የፍትህ ስርአቱ እንደዚህ ረክሶና ተዋርዶ እንደማያውቅ ተገንዝበንበታል። የሰራዊቱ፣ የደህንነቱና የፖሊሱ ሃይል የወያኔ አገልጋይነት በገሃድ የወጣው ከምርጫ 97 በኋላ ነው። ሰራዊቱ ከፖለቲካ ጌቶቹ በተሰጠው ትእዛዝ ሴት፣ ወንድ፣ ወጣት፣ አረጋዊ ሳይል በግፍ የተሞላ ጭፍጨፋና 15 ቀን ባለሞላ ግዜ ውስጥ ወደ መቶ ሽ የሚጠጋ ንጹህ ዜጋ ከየቤቱ በወድቅት ሰብስቦ፣ ትንሽ እንኳን ህጋዊ ማስመሰል በሌለበት ሁኔታ፣ በየቦታው አጉሯል። መገናኛ ብዙሃን እጅ እጅ የሚለውን የወያኔን ፕሮፓጋዳ በከፋ መልኩ ማሰራጨት የጀመሩት፣ የምርጫ ቦርዱ አይን ባወጣ የወያኔ ትእዛዝ አንደሚመራ የተረጋገጠው ቅንጅት እነዚህን ተቋማት በሚመለከት ያለውን አቋም ግልጽ አድርጎ ወያኔንን ለድርድር ከጠራ በኋላ ነው።

በመሆኑም ቅንጅት እነዚህን በቀጥታ በወያኔ ቁጥጥር ስር የዋሉ ተቋማት የሃገራችን የዴሞክራሲ ግንባታ እንቅፋቶች እንጂ አጋዦች አድርጎ እንደማያቸው ግልጽ መሆን አለበት። ዛሬ ቅንጅትን የገጠመው የስም ችግር፣ በነጻ የመንቀሳቀስ ችግር፣ አባለትን የማግኘትና የማሰባሰብ ችግር፣ ህዝብ ተቃውሞውን እንዲገልጥ ሰለማዊ ሰልፍ የመጥራት ችግር፣ ለህዝብ እምነቱንና አላማውን ለመግጽ፣ የሚሰነዘርበትን የሃሰት

ፕሮፓጋንዳ የሚመክትበት ዘዴ ማጣት ችግር፣ ሁሉም በአንድ ላይ ተደምረው በሃገሪቱ ነጻ ጸቋማት በላመኖራቸው የመጣ ችግር ነው።

እነዚህን ችግሮች በወያኔ ፍርድ ቤት፣ በምርጫ ቦርድና በሌሎችም ወያኔ በሚያዛቸው መንግስታዊ ተቋማት በኩል በመሄድ ማቃለል አይቻልም። "ፍርድ ቤቱና ምርጫ ቦርዱ ለወያኔ ወገንተኛ ናቸው" በማለት ይህ ችግር እንዲቃለል ህዝብ በደሙ ከከፈለና መሪዎቹም "በእነዚህ ተቋማት ጉዳይ ላይ መነጋገር ከማይፈልግ ገዥ ጋር በአንድ ፓርላማ ውስጥ አንታይም" ብለው ከተሰቃዩ በኋላ፣ ወደ ፍርድ ቤትና ወደምርጫ ቦርድ የስሙን ጉዳይ አንጠልጥሎ ቅንጅት መሄድ የሚችል አይመስልም። በእዚህ መንገድ መጓዙ የፖለቲካ፣ የዲፕሎማሲና የፕሮፓጋንዳ ጠቀሜታ አለው እንዳይባል፣ እነዚህ ተቋማት ከላይ እንዳተባለው በቀጥታ በወያኔ ትእዛዝ የሚዘወሩና የራሳቸው ህልውና የሌላቸው መሆኑን የማያውቅ ኢትዮጵያዊና የውጭ ሃገር ማህበረሰብ ያለ አይመስለኝም። እንደገና ፍትሃዊ ያልሆነ ውሳኔ እንዲወስኑ እናድርግና እናጋልጣቸው የሚል ከሆነም፣ አይሰራም። ተጋልጠው አብቅቷልና።

የቀረው መንገድ አንድና አንድ ብቻ ነው። የቅንጅትን ስም መሰረታዊ ከሆኑ የሃገሪቱ የዴሞክራሲ ችግሮች ጋር መታየት ያለበት መሆኑን መቀበል ነው። መፍትሄውም ስሙን ለማስከበር ወደፍርድ ቤትና ወደ ምርጫ ቦርድ መሄድ ሳይሆን ወይም ወያኔ ስለገፋን ብቻ ስሙን በሌላ ስም መቀየር ሳይሆን፣ መፍትሄው ፖለቲካዊ መሆኑን አምኖ የእዚህን ስምና የሌሎችንም መሰረታዊ የዴመክራሲያዊ ጥያቄዎች ባስቸኳይ ለመፍታት ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ወደ ውይይት እንዲመጣ ጥሪ ማድረግ ነው። በእብሪት ተሞልቶ እስቲ ምን ታደርጉኛላችሁ የሚል አምባገነን መንግስት ስልጣን በያዘበት ሃገር ላይ ይህንን ማሳካት ቀላል እንደማይሆን ግልጽ ነው። እንዲህ አይነቱን ሂደት በሃገራችን ለማስጀመር ስልጣን ላይ ባለው መንግስት ላይ ግፊት መፍጠር ያስፈልጋል። በሃገር ውስጥና በሃገር ውጭ የተቀነባበረ ትግልን ማድረግ ይጠይቃል።

- ይህ ትግል ከሁሉ በላይ ሰላማዊና ህጋዊ ትግሉን ለመምራት ሃላፊነቱን የተረከቡ አካላት ህገ-መንግስቱን የአለምአቀፍ ህጎችንና የተፈጥሮ ህጎችን ብቻ ተገን አድርገው በመንቀሳቀስ፣ ይህንንም መብታቸውን በመጠቀማቸው ህገወጥ በሆነ መንገድ በወያኔ አገዛዝ ለሚደርስባቸው ማናቸውም ጥቃት እራሳቸውን ማዘጋጀታቸውን በማረጋገጥ የሚጀመር ነው።
- ጉዳዩ የፖለቲካ ጉዳይ ስለሆነ መፍትሄው የፖለቲካው ስልጣን ያለው አካል ባስቸኳይ ምላሽ እንዲሰጠው መጠየቅ ነው። ይህ እስከሚሆን ድረስ የቅንጅት አመራር "ቅንጅት" የሚለውን ተገቢ ስሙን የሚጠቀም ይህንን በማድረጉ ለሚደርስበት አፈና ዝግጁ መሆኑን ግልጽ ማድረግ ነው።
- በሃገር ውስጥና በሃገር ውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊና አለምአቀፍ ህብረተሰቡ ከቅንጅት ስም ጋር ተያያዞ የተፈጸመው የወያኔ በእበሪት የተሞላ እርምጃ የተከናወነው ፍርድ ቤቱንና ምርጫ ቦርዱን ሽፋን በማድረግ ስለሆነ እነዚህና ሌሎችም የመንግስት አካለት ነጻ ሆነው ሳይደራጁ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ የዴሞክራሲ ሂደት መጀመር እንደማይቻል፣ ከፍርድ ቤትና ከምርጫ ቦርድ ውጭ የድርጅቱን ስም ለማስከበር ፖለቲካዊ መፍትሄ መሻቱ የዴሞክራሲ ትግሉ አካል እንደሆነ በማስረዳት፣ ለሀገራችን የፖለቲካ ችግር ሁሉን ያካተተ

የፖለቲካ መፍትሄ እንዲፈለግለት ለሚደረገው ትግል ድጋፋቸውን እንዲሰጡ ጥሪ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡

- በእንዲህ አይነቱ ፈታኝ ወቅት በድርጅቱና በመሪዎቹ ላይ ሊመጣ የሚችለውን ችግር አስቀድሞ በማየት በተለይ በ1998 በድርጅቱ ላይ ወያኔ የእመቃ እርምጃ በመውሰዱ ከተከሰተው ቀውስ በመማር ለቀጣዩ ትግል የሚያገለግሉ ዝግጅቶችን በጥድፊያ መስራት ይጠይቃል፡፡

## *4- ከድርጅቱ ህልውና መከበር ጋር ተያይዞ መነሳት የሚገባቸው የወደፊቱ የድርጅቱ የፖለቲካ አቅጣጫዎችና ስራዎችን*

ቅንጅት የፖለቲካ ፓርቲ ነው፡፡ የተቋቋመው ሰላማዊ፣ ህጋዊ፣ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ስልጣን ለመያዝና ሃገርና ህዝብን ይጠቅማሉ የሚላቸውን ፖሊሲዎቹን በስራ ላይ ለማዋል ነው፡፡ በመሆኑም ማኒፌስቶ ቀርጾ፣ በመርጫ 97 ተሳትፏል፡፡ የወደፊቱም አላማው ከእዚህ የተለየ አይደለም፡፡ ነገር ግን ቅንጅት በምርጫ 97 በመሳተፍ በሃገሪቱ ውስጥ ከፍተኛውን የህዝብ ድምጽ ቢያገኝም፣ ይህንን የህዝብ ድምጽ ማስከበር በእዚህ ድምጽ አማካይነት መያዝ የሚገባውን የመንግስት ስልጣን መያዝ አልቻለም፡፡ ይህ ሁኔታ ቅንጅት ከእዚህ በኋላ ወደ ምርጫ ለመግባትም ሆነ ህዝብንም እንዳለፈው ግዜ ተመዝገብና ምረጥ ለማለት የ97ቱ ምርጫ መሰረታዊ ድክመቶች ናቸው ያላቸውን ዘርዝሮ እንዲስተካከሉ ሃሳብ አቅርቧል፡፡ እነዚህም የቅንጅት መሪዎች ፓርላማ ለመግባት ያቀረቧቸው 8 ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ "በሃገሪቱ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲኖር፣ ህዝብ በምርጫ የሰጠው ድምጽ እንዲከበር፣ አብላጫውን የህዝብ ድምጽ ያገኘው ፓርቲ መንግስታዊ ስልጣን እንዲረከብ፣ መሰረታዊ የሆኑት የመንግስት ተቋማት ማንም ፓርቲ ባልወገነ መንገድ በሁሉም የፖለቲካ ሃይሎች ድርድርና ስምምነት ነጻና ገለልተኛ ሆነው መቋቋም እንዳለባቸው" የሚጠይቁ ናቸው፡፡

አሁን ባላንበት ሁኔታ አነዚህ ተቋማት በ1997 ምርጫ የነበራቸው አስመሳይ ነጻነት ጠፍቷል፡፡ የለየላቸው የአምባገነናዊ ስርአት የአፈና መሳሪያ ሆነዋል፡፡ በሃገራችን የነበረው አስመሳይ ዴሞክራሲም 1997 ከነበረበት ሁኔታ ተገፍቶ ቦታውን ለለየለት አምባገነናዊነት ለቅዋል፡፡ ከወዲሁ ግልጽ መደረግ ያለበት ጉዳይ በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ በቅርብም ይሁን በእሩቁ በሚደረጉ ምርጫዎች ቅንጅት መሳተፍ የማይችል መሆኑን ነው፡፡ ቅንጅት በየአምስት አመቱ ህዝብን ለምርጫ እየቀሰቃሰ ደግፉኝ እያለ፣ በየአምስት አመቱ ቅንጅትን የደገፉ የሚገደሉበትን፣ የሚታሰሩበትን፣ የሚቀጠቀጡበትን፣ የሚፈናቀሉበትን፣ ከሃገር የሚሰደዱበትን፣ በረሃብ የሚሰቃዩበትን፣ በዜግነታቸው ማግኘት የሚገባቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት የሚከለከሉበትን ሁኔታ በግድየለሽነት እየፈጠረ፣ ወያኔ አምባገነናዊ ስጋውን በዴሞክራሲ አልባሳት ለማሳመር በሚጠራው ምርጫ ሁሉ የሚሳተፍ ድርጅት አለመሆኑን ግልጽ ማድረግ ይገባል፡፡

ከእዚህም በላይ ሁኔታው ከቅንጅት ቁጥጥር ውጭ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ከመንግስት ባለስጣልናት አስተሳሰብ ውጭ የራሳቸው እምነት ያላቸውን ዜጎች ለመሰለል ዴሞክራሲን በርካሽ መሳሪያነት የተጠቀመ መንግስት በስልጣን ላይ ተቀምጧል፡፡ ወያኔ፣ የተቃዋሚ ፓርቲ ቢሮዎችን በመስበር የአባላትን ሰምና አድራሻ የያዙ ዶሴዎችን በመዝረፍ፣ ሰውን በየቤቱ በገጠርና በከተማ እየለቀመ ለመግደልና ለማሰር ለማስፈራራት ችሏል፡፡ በእንዲህ አይነቱ የቅንጅት ደጋፊዎች ከምርጫ 97 በፊት

እንደታዘብነው በአባልነት ለመመዝገብና የአባልነት መዋጮ ለመክፍል ዛሬም ተመልሰው እንደ ቀድሞው ወደ ቅንጅት ቢሮ እንደማይጎርፉ ግልጽ ነው። ይህ እንደማይደገም ዋስትናው ምንድነው ብለው መጠየቃቸው አይቀርም። እንደምናስታውሰው ለምርጫ 97 በየገጠሩ ቅንጅት ለቅስቀሳ በወጣ ቁጥር የኢትየጵያ አረሶ አደሮች ወያኔ በምረጫ ካርድ ለመውረዱ የነበራቸውን ጥርጣሬ በማያሻማ ቋንቋ ገልጸው ነበር። በወያኔ የተወሰደው አፈና የድርጅቱን የተወሰኑ የላእላይ ምክር ቤት አባላት ሳይቀር "በእንዲህ አይነቱ አፋኝ ሁኔታ ለመስራት አንችልም፣ የለንበትም" የሚል ውሳኔ ያስደረሰ ነው። ይህ የሚያሳየው ማንም ሰው በሃገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ በመሳተፉና ስልጣን ላይ ካለው ፓርቲ የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ስላለው ብቻ ህይወቱ፣ አካሉ ንብረቱና ደህንነቱ አደጋ ላይ የሚወድቅ መሆኑን መረዳቱን ነው። ይህ እንዳይሆን ዋስትና የሚሰጡት ስልጣን ላይ ያሉ ገዥዎች አይደሉም፣ ወይም ግድ የላችሁም ምርጫ ግቡ በማለት ዴሞክራሲን የረጅም ግዜ ጉዞ ውጤት አድርገው በማስረዳት አላማቸው ግን ጥቅማቸውን የሚያስከብረውን የወያኔ መንግስት እንዳለፈው ግዜ በተጭበረበረ ምርጫ ስልጣን ላይ ለማቆየት ፍለጎቱ ያለቸው አንዳንድ የውጭ መንግስታት አይደሉም።

በሃገራችን የሚካሄድ ምርጫ ዴሞራሲያዊነትና በምርጫው የሚሳተፉ ዜጎች የመብት ዋስተና ቅንጅት ካቀረባቸው ነጻ ተቋማት ውጭ የሚመጣ አይደለም። ይህንን ለማድረግ የሚጠይቀው የፖለቲካ ጽናት ብቻ ነው። ይህ የፖለቲካ ጽናትና ፍላጎት በተለይ በገዥው ፓርቲ እጅ እስካለ ድረስ እነዚህን ተቋማት ህዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ አመኔታ የሰጧቸው ተቋማት አድርጎ ለማቆምና ስራቸውን ለማስጀመር ቀላል ነው። ተቋማቱ በሰለጠነ የሰው ሃይልና በስራ ልምድና ባህል ተገንብተው ተመሳሳይ ተቋማት በሌሎች ያደጉ ሃገሮች ውስጥ ለህብረተሰቡ መስጠት የሚችሉትን የዳበረ ግልጋሎት በሀገራችን ለመስጠት ግዜ ሊፈጅባቸው ይችላል። ግንባታውን ለመጀመር ግን መቶ አመት የሚያስጠበቅ ምክንያት አይኖርም። በግንባታው ስራ ማናቸውንም እገዛ ለማድረግ ተዘጋጅተው የሚጠብቁ፣ አሁንም የሚሰራ መስሏቸው በአቅም ግንባታ ስራ ከፍተኛ ነዋይ የሚያፈሱ ለሃገራችን በጎ ምኞት ያላቸው የውጭ መንግስታት አሉ። ወያኔንና ደጋፊዎቹን እንደ አበደ ውሻ ያደረጋቸው በአሜሪካን ኮንግረስ አልፎ አሁን ለሴኔቱ የቀረበው HR2003 ከእዚህ የተለየ አለማ የለውም።

የፖለቲካ ፍለጎቱ ካለ እነዚህን ነጻ ተቋማት በእግራቸው እንዲቆሙና እንዲንቀሳቀሱ ለማድርግ የሚያስፈልገው ግዜ በጣም አጭር ነው። ከእዚህ በተጨማሪ እውቀቱና ሃብቱ በቀላል የማይገመተው በውጭ የሚኖረው በርካታ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ የሀገሪቱን ቁልፍ የዴሞክራሲ ችግሮች ለመፍታት ስምምነት ካለ ሁለንተናዊ ድጋፉን ለመስጠት ዝግጁ እንደሆነ ባለፈው ሁለት አመት ለሰብአዊ መብቶች፣ ለህግ መከበርና ለዴመክራሲ መስፈን ባደረገው ከባድና አኩሪ ተጋድሎ አረጋግጦታል።

"የወያኔ ባለስልጣናት በምርጫ 97 ለውድቀት ካበቃን ተመክሮ በመነሳት ትምህርት ተምረን ማስተካከያዎች አድርገናል" ሲሉ ይደመጣል። እነኚሁ ባለስልጣናት "የቅንጅትን አባላት ሳይቀር አሳምኜ የድርጅቴ አባላት አድርጊያለሁ። የተጠናከረ በብዙ ሚሊዮኖች አባላት የተሞላ ድርጅት አቁሚያለሁ። የቅንጀትን ምንነት ለአብዛኛው ህዝብ በመግለጽ እኩይ ድርጅት እንደሆነ እንዲረዳ አድርጌአለሁ" ይሉናል። ይህ እውነት ከሆነ ኢህአዴግ ሁሉም ፓርቲዎች የተስማሙበትን መሰረታዊ የሆኑትን የነጻ ተቋማት ምስረታ ስራ ጥየቄ ለመመለስ የሚፈራበት ሁኔታ ሊኖር አይገባውም። ግን የምናየው ከእዚህ የተለየ

ነው። የገዥው ፓርቲ ሌላው ቀርቶ የውጭ ታዛቢዎች እንኳን እንደ97ቱ ምርጫ በሚቀጥለው ምርጫ እንዲገኙ አልፈቅድም ብሏል። ከእዚህ አልፎ በረከት ስምኦንን የመሰለው ከፍተኛ የወያኔ ባለስልጣን "ቅንጅት እንደ 1997ቱ አይነት እድል አግኝቶ እንዲንቀሳቀስ አንፈቅድለትም" ሲል በውል መደመጡ የሚያሳየው ነገር ቢኖር አሁንም ቅንጅት ወያኔን እንቅልፍ የሚነሳው እንደሆነ፣ አሁንም የቅንጅት ጥላ ወያኔን እንደሚያስበረግገው የሚያሳይ ነው። "ነጻ ተቋማት ተቋቁመው፣ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ቢደረግ ከስልጣን እባረራላሁ" የሚል ተጨባጭ ስጋት የተጠናወተው ወያኔ ለእነዚህ ተቋማት መመስረት ቅን ፍላጎት እንደማይኖረው ግልጽ ነው።

ያለንበትን የፖለቲካ አጣበቂኝ በአጭሩ እንደሚቀጥለው ማቅረብ ይቻላል። ቅንጅትና የኢትዮጵያ ህዝብ "ያለነጻ ተቋማት በኢትዮጵያ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ አይኖርም የህዝብ ድምጽ አይከበርም" የሚል ጠንካራ እምነት አላቸው። ለእዚህም ፍጹም ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ህገ-መንግስቱን ተገን አድርገው መንቀሳቀስ ከጀመሩ ሰንብተዋል። በሌላ በኩል "ነጻ ተቋማት ተመስርተው ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ቢደረግ በመላ ሃገሪቱ፣ ልክ በ1997ቱ ምርጫ በአዲስ አበባ እንደታየው፣ አንድም ሰው ማስመረጥ አልችልም" የሚል ጥኑ ፍራቻ የተጠናወተው ወያኔ/ኢህአዴግ አለ። በተለይ በቅርቡ የቀድሞዎቹ የህወሃት አመራሮች ያቆሙት የነገብሩ አስራት ፓርቲና ሌሎችም ድርጅቶች ነጻና ፍትሃዊ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው ትግራይ ውስጥ ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቡ ከሆነ፣ ኢህአዴግ በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ ማንንም፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን መለስ ዜናዊን ጨምሮ ማስመረጥ እንደማይችል ያውቀዋል። በመሆኑም በአመጽ የተደገፈ፣ ህጋዊ ያልሆነ ህገ-መንግስቱን የሚንድ እርምጃ መውሰዱን በመቀጠል ወያኔ ስልጣን ላይ ለመቆየት እየተንቀሳቀሰ ነው።

ወያኔ ኢህአዴግን የቆጥ የባጡን በሃገርና በህዝብ ስም እየቀባጠረ፣ በማጭበርበር በመዋሸት ክቡርና ብርቅ የሆኑ ማህበራዊ እሴቶችን በማርከስ፣ በመግድል በማሰር፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ዘለቄታዊ ሃገራዊ ጥቅም የሚጎዳ፣ ለግዜው ግን ስልጣን ላይ ለመቀጠል የሚያስችል አሳፋሪ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ይዞ እንዲንቀሳቀስ የሚያደርገው በህዝብ ፊት ቀርቦ፣ በህዝብ ለመዳኘት ቢመርጥ፣ ውጤቱን አስቀድሞ ስለሚያውቀው ነው። ውጤቱ አሳፋሪ ሽንፈት ነው።

በተለይ ስልጣን ላይ ብዙ ሲቆይ ከሚደነዝዝና የራሱን ህልም እውነታ አድርጎ ከሚያይ የታመመ የገዥዎች ህሊና በመነሳት፣ ወያኔ/ኢህአዴግ በ1997 የከፈታት አስመሳይ የዴሞክራሲ ጨዋታ ክፉኛ ከለበለበችው በኋላ "ምርጫ" ሲሉት፣ "በተለይ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ" ሲሉት እንደሚበረግግ ማወቅ ያስፈልጋል። ይህንን እያወቀ በውዴታ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ የሚደረግበትን፣ ጠንካራ ተቃዋሚ የሚፈጠርበትን ሁኔታ ወያኔ ይፈጥራል ብሎ የሚያስብ የሚኖር ካለ ተላላና ተስፈኛ ብቻ ነው። ጥያቄው ከእንዲህ አይነቱ አጣብቂኝ እንዴት ይወጧል ነው።

<u>ከሁሉ በፊት በሃገራችን የዴሞክራሲ ትግል ስለሚደረግበት የፖለቲካ ሁኔታና ይህ ስለሚጠይቀው የስነ-ልቦናና ሌሎችም ዝግጅቶች የጠራ አቋም መያዝ ያስፈልጋል። በመሆኑም፤</u>

- በገዥው ፓርቲ ምንነት ወይም ባህርይ ላይ ግልጽ ግንዛቤ ልንይዝ ይገባናል። ትግል እየተደረገ ያለው ምንም አይነት ዴሞክራሲያዊ ዝንባሌ ከሌለው አምባገነን

መንግስት ጋር ነው። በእዚህ ላይ ብዥታ ሊኖር አይገባም። ከእንዲህ አይነቱ መንግስት መብትን በልመና፣ በመማጸንና ጠባይ በማሳመር አይገኝም። የአምባገነኖች ዋናው መለያ በተለመኑ፣ በተጋበዙና ተማጽኖ በቀረበላቸው ቁጥር እብጠት የሚሰማቸው፣ የበለጠ በአምባገነንነታቸው የሚኮፈሱ መሆናቸው ነው። ከምርጫ 97 በፊትና በኋላ የተቃዋሚው ልመናና ተማጽእኖ ወያኔንን በእብሪት የተሞላ እርምጃ ለመውሰድ ያበረታታው መሆኑን መዘንጋት አይገባም። በእዚህ የወያኔ ባህርይ ላይ በቂ ግንዘቤ ከሌለ ለወደፊቱ ካለፈው የበለጠ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ይሆናል። እስካሁንም ወያኔ ለዴሞክራሲ በሚደረገው ትግል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማድረስ የቻለው ተቃዋሚዎቹ አምባገነናዊ የሆነው ባህርዩን ተረድተው ከእንዲህ አይነቱ ሃይል ጋር ለሚደረግ ትግል የሚያስፈልገውን ሁለንተናዊ ዝግጅት ለማድርግ ባለመቻላቸው ነው።

- ነጻነት፣ የልመናና የተማጽእኖ ውጤት ሳይሆን ሰዎች በሰውነታቸው፣ ዜጎች ደግሞ በዜግነታቸው የሚጎናጸፉት መብት መሆኑን በመረዳት ትግሉ ነጻነትንና መብትን ለማስከበር እንጂ የነጻነትና የመብት እርጥባን ከወያኔ ለመቀበል እንዳልሆነ ማወቅና ማሳወቅ ይጠይቃል።
- ትግሉ በአንድ በኩል በሃገራችን የፖለቲካ እድገት ደረጃ ሲለካ በጣም ኋላ ቀር አመለካከትና እምነት ካላው የፖለቲካ ቡድን ጋር መሆኑን፤ ትግሉ በሲቪልና በወታደራዊ ቢሮክራሲው ውስጥ የተሰገሰጉ በራሳቸው መተማመን ከሌላቸው በችሎታና በጥረት ሳይሆን ከዘር ቆጠራ፣ በዘመድ አዝማድ፣ በአበልጅነት፣ በጓደኝነትና በዘረፋ በተሳሰሩና፣ በፖለቲካ ሎሌነታቸው የሚገኝን ፍርፋሪ እየለቀሙ መኖር በመረጡ ግለሰቦች ከተሞላ ኋላ-ቀር መንግስታዊ ስርአት ጋር መሆኑን፤ ትግሉ "ግደሉና እሰሩ" ሲባሉ "ለምን" ሳይሆን "ስንት እንግደልና ስንት እንሰር" ከሚሉ ጄሌ ጀነራሎች፣ "ፍረዱ" ሲባሉ "የሞት ወይንስ እድሜ ልክ በማለት የፖለቲካ ጌቶቻቸውን" የሚጠይቁ፣ ፍትህን የመሰለ ክቡር ነገር በማራከሳቸው ህሊናቸውን የማይቆረቁራቸው ዳኞች ጋር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።
- ትግሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቱ ኋላ ቀር በሆነ ሃገር ውስጥ አሁንም ከ85 በመቶ የሚሆነው ህዝብ በስፋት ተበትኖ በገጠር በሚኖርበትና ለመንግስት የአፈና መዋቅሮችና ካድሬዎች ጥቃት በቀላሉ በተጋለጠበት ሃገር ነው። ይህ ደሃ አርሶ አድር የህብረተሰብ ክፍል በጋራ ለሚደረግ ሃገራዊ የህዝባዊ ሰላማዊ እምቢተኛነት ትግል ያለተመቻቸ አሰፋፈርና አኗኗር ያለው ነው። ትግሉ ለሰላመዊና ህጋዊ ትግል ወሳኝ የሆነ ሚና መጫወት የሚችሉ መንግስታዊና ማህበራዊ ተቋማት የእድገት ደረጃ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ በሆነበት ሃገር የሚካሄድ ነው። አሉ የሚባሉትም ትልልቅ መኀበራዊ ተቋማት፣ የሰራተኛና የመምህራን መህበራት አይነቶቹ፣ በወያኔ እመቃ ጫጭተዋል። በአገልግሎትና በፋይናንስ፣ በኢንደስትሪ ምርትና በንግድ ስራዎች ላይ የተሰማራው የሰው ሃይል ቁጥሩ በጣም አነስተኛ ነው። በአጠቃላይ ትግሉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉልበቱ ባልፈረጠመ፣ በተደራጀ መንገድ ለረጅም ግዜ የሚቀጠል የሰላመዊ ተቃውሞ፣ ለምሳሌ ቤት ውስጥ መቀመጥን ስራ ማቆምን መሸከም በማይችል፣ በፍርሃት እንዲሸበብ ተከታታይ ገዥዎች ግፍና መከራ ባዘነቡበት ህብረተሰብ ውስጥ የሚካሄድ መሆኑን ጠንቅቆ ማወቅ ይጠይቃል።
- ከላይ የተባለውን በመሉ ግምት ውስጥ በማስገባት የትግሉ ዋና ሸክም ህዝብ በ1997ቱ ምርጫ የመብቱ፣ የጥቅሚና የህልሜ ወኪሎች ናቸው ብሎ

በአመናቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና በተለይ ደግሞ በእነዚህ ድርጅቶች መሪዎች ላይ የተጫነ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። በሃገራችን በሰፈነው ከፍተኛ አፈና የተነሳ ህዝብ ለትግሉ ድጋፍ እንዲያደርግ ጥሪ ማድረግና ህዝብም ለጥሪው ምላሽ መስጠት የሚችልበት ህገ-መንግስታዊ መብቶች በተገደቡበት ሁኔታ የሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች፣ ትግሉን ወደፊት መግፋት የሚችሉት በዋንኛነት በራሳቸው የፖለቲካ ጽናት፣ ብግለሰብና በቡድን ደረጃ በሚወስዱት የሰላማዊ እምቢተኛነት አቋሞች፣ በቡድንና በግለሰብ ደረጃ ለእነዚህ አቋሞች በሚከፈል ከፍተኛ መስዋእትነት ነው።

- በኢትዮጵያ የሚደረግ ሰለማዊ እና ህጋዊ ትግል ሁሌም በምሳሌነት በምንጠቅሳቸው ዩክሬንና ጆርጅያ ውስጥ እንደተደረጉ ወይም ህንድን ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት በማህተመ ጋንዲ እንደተመራው የሰላማዊ የነጻነት እንቅስቃሴ ጋር በማመሳሰል ከፍተኛ ስህተት ከመስራት መጠንቀቅ ይኖርብናል። በእነዚህ ቦታዎች የተቃዋሚ መሪዎች ህዝብን ለሰላመዊ ህዝባዊ እምቢተኛነት ማንቀሳቀስ የቻሉት ሌላው ቢቀር የህግ የበላይነት የሰፈነበት፣ የፖለቲካ ባለስልጣናቱ የሚያስተላልፉትን ህገወጥና ኢሰብአዊ ትእዛዝ ላለመፈጸም በራስ መተማመኑ፣ ድፍረቱ፣ እውቀቱና ብቃቱ ባላቸው ከፍተኛ የወታደራዊና የፖሊስ መኮንኖች በአሉበት ሀገር ውስጥ እንደሆነ ልብ ማለት ይገባል። የሰው ልጅ ህይወትና የግል ንብረት የተከበሩ መሆናቸውን የተቀበለ ማህበራዊ ህሊና በሰፈነበት፣ በእዚህ ማህበራዊ ህሊና ላይ የተገነባ መንግስታዊ ስርአት ባለባቸው ሃገሮች ውስጥ የተካሄደ ነው። ህንድ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛትነቷ የእንግሊዝ አካል ስለነበረች የእንግሊዝ የፖለቲካ ስርአት የደረሰበት የእድገት ደረጃና በወቅቱ በእንግሊዝ የነበረው የፖለቲካ ሁኔታ በአንድ ላይ ተደምረው፣ ማህተመ ጋንዲ ሰላማዊ ትግል ማድረግ እንዲችል በጣም የተመቻቻ ሁኔታ እንደፈጠሩለት መዘንጋት የለብንም። የተለያዩ በታሪክ የሚታወቁ ሰላማዊ ትግሎች በሙሉ፣ በአሜሪካን ሃገር በማርቲን ሉተር ኪንግ የተካሄደውን የሲቪል መብቶች የማስከበር እንቅስቃሴ ጨምሮ፣ በራሰቸው የታሪክ የፖለቲካ የባህል ነባራዊ እውነታና ማእቀፍ ውስጥ የተከናወኑ መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል ለማለት ነው። በሌሎች ሃገሮች ውስጥ የተከናወነውን ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ሳናገናዝብ በስራ ላይ እናውል ብንል የሚያዋጣ አይሆንም። ሌላው ቢቀር በ1960ዎቹና 1970ዎቹ የሃገሪቱ የፖለቲካ ልሂቃን የኮምኒስት ርእየተ- አለምን በጭፍን በመኮረጅ ካደረሱት ጥፋት መማር ይኖርብናል። የእኛ ሀገር ሁኔታ የተለየ ነው። በሃገራችን ስለሰው ልጅ የህይወት ክቡርነት ምንም የማይሰመው መንግሰት ነግሷል። ሰለማዊ ተቃዋሚን በሽዎች የሚገድል ትእዛዝ ማስተላለፍ፣ ይህንን ትእዛዝ ለመፈጸም ወደ ኂላ የማይሉ የጦር የስለላና የፖሊስ መኮንኖች ያሉት መንግስት ነው። አንድ ግለሰብ በመንግስት ላይ ያለኝን ተቃወሞ የግል የንግድ ድርጅቴን በገዛ ኪሳራዬ በመዝጋት ወይም የግል ታክሲዬን ባለማንቀሳቀስ ህገ-መንግስታዊ መብቴን በመጠቀም እገልጻለሁ ለማለት እንደማይችል ጥቅምት 1998 ወያኔ ከወሰደው እርምጃዎች አይተናል። ጥቅምት 1998 ቅንጅት የጠራውን የቤት ውስጥ መቀመጥ የተቃውሞ ጥሪ የደገፉና ሱቃቸውን የዘጉ ነጋዴዎች፣ ሱቃቸውን ደግመው እንዳይከፍቱ ሲደረጉ፣ ታክሲያቸውን በቤታቸው አቁመው የነበሩ ግለሰቦችን ቤታቸው ውስጥ በመግባት ሽጉጥ ጭንቅላታቸው ላይ በማድረግ ታክሲያቸውን በማሰፈራራት ከቤታ አውጥተው

አንዲያሸከረክሩ መደረጋቸውን አረጋግጠናል፡፡ ለእዚህ ነው በእንዲህ አይነቱ አፋኝ ሁኔታ ውስጥ የሚካሄድ ትግል ከማንኛውም ጉዳይ በላይ በትግሉ መሪዎች ተክለ-ሰውነት፣ አርአያነትና ከፍተኛ መስዋእትነት ላይ የሚገነባ መሆኑን አስቀደሞ ጠንቅቆ መረዳት የሚጠይቀው፡፡ በሃገራችን የሚካሄደው ትግል ተመሳሳይ በሆነ መንገድ በሌሎች ሃገሮች ከተካሄደው ሰላማዊ ትግል ጋር ሲነጻጸር አጅግ አስቸጋሪና የተወሳሰበ ነው፡፡ በከፍተኛ ጥበብ፣ እውቀት፣ የፈጠራ ችሎታ፣ አርቆ አሳቢነት፣ ጥብቅ ስብእና ድፍረት ላይ የሚመሰረት ነው፡፡ የወያኔን የአፈና መዋቅር መቋቋም የሚችል አደረጃጀት፣ ወያኔ በሞኖፖል የያዛቸው የሚድያ አውታሮች የሚያሰራጭቱን የሃሰት ፕሮፓጋንዳ መመከትና ለህዝብ መረጃ ማድረስ የሚቻልባቸውን ዘዴዎች በጥንቃቄ በማጥናት ስራ ላይ ማዋል ይጠይቃል፡፡ በሃገር ውስጥና በሃገር ውጭ በእቅድ የሚመራ የማያቋርጥ፣ የተቀነባባረና በሚገባ የተደራጀ የዲፕሎማሲ ስራ መስራት ይፈልጋል፡፡ እነዚህ ስራዎች በሙሉ በድፍረትና በእልህ በተሞላ የሰለማዊና የህጋዊ አምቢተኛነትን እንጂ የወያኔን በጎ ፈቃድ በማግኘት የሚከናወኑ አለመሆናቸውን መገንዘብ ይጠይቃል፡፡ በመጨረሻም ትግሉን ለመምራት በተሰባሰቡ ግለሰቦች መሃከል ጥልቀት ያለውን ፍቅር፣ አንድነትና መተሳሰብ የግድ የሚል ነው፡፡

- ይህ ትግል ህገ-መንግስታዊ መብቶችን ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ የሚጥስ፣ ነጻ ያለሆኑ ፍርድ ቤቶችንና ሌለች ነጻ ያለሆኑ አካላትን ህገ-መንግስታዊ ብሎ ከሚያሞካሽና በስማቸው ወንጀል ለመፈጸም ወደኋላ ከማይል ወያኔ/ኢህአዴግን ከመሰለ ጭራቅ ጋር የሚደረግ ነው፡፡ የትግሉ አንዱ ገጽታ፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ወያኔ በእነዚህ ህገወጥ ተቋማቱ የሚያስወስናቸውን ውሳኔዎችና ትእዛዞች ባለማክበር፣ ሰለማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ህገ-መንግስቱንና አለምአቀፍ ህጎችን ተገን አድርጎ መንቀሳቀስን ይጠይቃል፡፡ አሁን ባለንበት ሁኔታ እንዲህ አይነቱን የሰላማዊ እምቢተኛት የተቃወሞ ትግል በአርአያነት መምራት የሚችሉት የቅንጅትና የሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎች ናቸው፡፡ ባለንበት ወቅት የወያኔ የአፈና ጽልመት በሃገራችን ህዝብ የነጻነት ፍለጎት ላይ አስከፊ ጥላውን እንዳያጠላ፣ በህዝብ ልብ ውስጥ ምርጫ 97 የጫረው የነጻነትና የዴሞክራሲ መንፈስ እንዳይዳከም፣ የቅንጅት መሪዎች በግልና በቡድን የሚያደርጉት የሰላማዊ እምቢተኛነት እንቅስቃሴ የሚወስነው ነው፡፡ በቅድሚያ ግን ይህ እንቅስቃሴ የሚያስከፍለው መስዋአትነት ቀላል እንዳልሆነ በሚገባ መታወቅ አለበት፡፡

<u>በተግባር ደረጃ፡፡</u>

ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው የቅንጅት ተግባራት ወደፊት በምርጫ መሳተፍ የሚችልባቸውን ሁኔታዎች በአስቸኳይ ማሟለት ነው፡፡ የቅርብንም ይሁን የሩቅ ምርጫ ለማሳተፍ የድርጅቱ ስም ህገዊነት መከበር ይኖርበታል፡፡ ድርጅቱ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲኖር አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመናቸው ተቋማት ጥያቄ ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡

<u>በፖለቲካ መስኩ፤</u>

- በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ቀደም በለው በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ሁሉንም የፖለቲካ ፓርቲዎች ያካተተ ውይይት እንዲጀምር፣ ይህ ውይይት የሚወስደውን

ግዜና የተባሉትን ነጻ ተቋማት ለመመስረት ሊወስድ ከሚችለው ግዜ አንጻር ለእዚህ ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶት በፍጥነት መንቀሳቀስ ካለተቻለ ምርጫ 2010 ነጻና ፍትሃዊ እንደማይሆን፣ የነጻና የፍትሃዊነት ዋስትና በሌለበት ሁኔታ ቅንጅት በምርጫ የመሳተፍ ሀሳብ እንደማይኖረው በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ህዝብም በምርጫ መሳተፍ እንደማይኖርበት እንደሚያስተመር ግልጽ በማድረግ ስልጣን ላይ ላለው መንግስት የማያሻማ መልእክት ማስተላለፍ፤

- ይህንን አቋም በጠቅላላ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማሳወቅ፣ የነጻ ተቋማት አጀንዳ፣ ዋናው የዴሞክራሲ ትግሉ የሚሽከረከርበት የትግል አጀንዳ መሆኑን ለህዝብ በማስረዳት ፣የነጻ ተቋመት ምስረታ ጥያቄ ምላሽ ማግኘት በታሪካችን ትልቁ የዴሞክራሲ ድል መሆኑንና ሌሎች የፖለቲካ አጀንዳዎች በሙሉ ከእዚህ አጀንዳ በታች እንደሆኑ መግለጽ፤
- በተመሳሳይም በሃገር ውስጥና በሃገር ውጭ ለሚገኙ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች ትግላቸው በእዚህ አጀንዳ ዙሪያ እንዲሆን፣ በሃገር ውስጥ ሆነ በውጭ በሚደረጉ የሳለማዊ ሰልፎች፣ በሚጠሩ ስብሰባዎች፣ የትግሉ ወሳኛ አሰባሳቢ አታጋይ መፈክር <u>"ነጻና ዴሞክራሲ ተቋማት በሃገራችን ይመስረቱ"</u> የሚለው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። <u>"ዳኞችና የፍትህ ስርአቱ ከገዢው ፓርቲ ነጻ ይሁኑ።"</u> <u>"የመከላከያ የደህንነትና የፖሊስ አካላት ከገዥው ፓርቲ ነጻ ይሁኑ።"</u> <u>"በመንግስት ስም በገዥው ፓርቲ የተያዙት የመንገስት መገናኛ ብዙሃን ነጻ ሆነው ይደራጁ።"</u> <u>"የሚድያ ነጻነት አሁኑኑ"</u> <u>"ያለነጻና ገለልተኛ ምርጫ ቦርድ ነጻና ፍትሃዊ መርጫ አይኖርም"።</u> <u>"የቅንጅን ስም እና ህልውና ለማጥፋት የሚደረገው ህገ ወጥ ደባ አሁኑኑ ይቁም።"</u> የመሳሰሉት መፈክሮች ኢትዮጵያውያን በሚኖሩበትና በሚሰሩበት በሁሉም አለም እንዲያስተጋቡ ማድረግ፤
- በሃገራችን ውስጥ የሚገኙና በሃገራችን ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲኖር ቁልፍ የሆኑት የመንግስት ተቋማት በስልጣን ላይ ካለው መንግስት ነጻ ሆነው መደራጀት አለባቸው ከሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በአስቸኳይ ወይይት በመጀመር የጋራ አቋም በመያዝ በጋራ ትግል ለማድረግ መስማማት፤
- ከእዚህ ውጭም በተለያዩ ሰበቦች ወያኔ በሃገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይሳተፉ ያደረጋቸው፣ በእዚህም የተነሳ ህጋዊና ሰለማዊ በሆነ መንገድ መንቀሳቀስ ያልቻሉ ማናቸውም ድርጅቶች በሃገራችን መፈጠር ያለባቸው ነጻ ተቋማት የሃገራችንን የፖለቲካ ችግሮች ለመፍታት ቁልፍ መሆናቸውን ተረድተው እነዚህ ተቋማት እንዲመሰረቱ ቅንጅት የሚያደርገውን ሰላማዊና ህጋዊ ትግል እንዲያግዙ ጥሪ ማድረግ ያስፈልጋል። በሃገራችን ፖለቲካ ውስጥ በመሳሪያ ሃይል የተደገፈ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ድርጅቶች በሙሉ፣ በስልጣን ላይ ያለውን የወያኔ መንግስት ጨምሮ የጦር መሳሪያቸውን ከፖለቲካ አውጥተው ለሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች በነጻነትና በእኩልነት መንቀሳቀስ እንዲችሉ በሚያደርግ የፖለቲካ መስክ ላይ ሰለማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ መወዳደር ማድረግ የሚችሉበት ሁኔታ ለመፍጠር ቅንጅት የሚያደርገውን ጥረት እንዲደግፉ ጥሪ ማድረግ። እንዲህ አይነቱን ጥሪ ማቅረብ ህገ-መንግስታዊ መብት መሆኑን፣ ለእነዚህ ሃይሎች ጥሪ ማድረግ፣ ከእዚህ ሃይሎች ጋር በወኪሎቻቸው አማካይነት ለለሰላም፣ ስለዴሞክራሲና ስለእርቅ መነጋገር ለመለስ ዜናዊና ለወያኔ ድርጅት በግል የተሰጠ መብት አለመሆንን፤ ከጥቂት ወራት በፊት መለስ ዜናዊ በቀጥታ ከኦነግ መሪዎች ጋር ያደረገውን አሁንም

በቅርቡ በሽማግሌዎች አማካይነት ወይይት ለማድረግ ሞክሮ የከሸፈውን ሙከራ በዋቢነት በመጥቀስ በድፍረት መንቀሳቀስ ይጠይቃል፡፡

<u>በደፕሎማሲያዊ መድርኩ</u>

- በሃገር ውስጥ ለሚገኙ የአለምአቀፍ ማህበረሰብ ወኪሎች ቅንጅት ያነሳውን ጥያቄ ቁልፍነት በማስረዳት ለእዚህ ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ድጋፋቸውን እንዲያደርጉ፣ ቅንጅትን የመሳሰሉ ሰላማዊና ህጋዊ የፖለቲካ እንቅስቀሴ ለማድረግ ቆርጠው የተነሱ ድርጅቶችን ማፈን፣ ለሚያነሷቸው መሰረታዊ የዴሞክራሲና የፍትህ ጥያቄዎች መልስ አለመስጠት በሃገራችን ሊያስከትል የሚችለውን የፖለቲካ ቀውስ መግለጽ፣ በእዚህም ቀውስ የራሳቸው ብሄራዊ ጥቅም ሳይቀር ጉዳት ሊደርስበት የሚችል መሆኑን በሚገባ ማስረዳት፣
- በውጭ ሃገር የሚገኙ የድጋፍ ድርጅቶችንና እንዲሁም የቅንጅት ፓርቲ ልኡካኖችን በመጠቀም በወያኔ ላይ ተጽእኖ ማድርግ የሚችሉትን የውጭ መንግስታት ሎቢ ማድረግና ድጋፍ ማሰባሰብ ሊተኮርበት ይገባል፡፡

ማጠቃለያ

የእዚህ ጽሁፍ አላማ አጠቃላይ ከሆኑ ጉዳዮች በማለፍ በስራ መተርጎም ይገባቸዋል ብዬ የማምንባቸውን ነጥቦች በዝርዝር ለማቅረብ ነበር፡፡ ይሁንና ዝርዝር ስራዎችን የሚመለከተው ጽሁፍ የድርጅቱ የውስጥ ሰነድ ሆኖ ድርጅቱ በውስጡ የሚወያይበት ቢሆን ይሻላል የሚል እምነት አደረብኝ፡፡ በተጨማሪም ይህንን የተለየ ይዘት ያለውን ተጨማሪ ጽሁፍ ጠቅላላ የአመለካከትና የአቅጣጫ ነጥቦች ከሚያነሳ ጽሁፍ ጋር መቀላቀሉ ችግር የሚፈጥር መሰለኝ፡፡ በወጉ መደረግ የሚገባውን ውይይት ያደፈርሰዋል ብዬ አሰብኩ፡፡ በመሆኑም የድርጅትን፣ የፕሮፓጋንዳና የገንዘብ እርዳታን ማሰባሰብ የመሳሰሉ ስራዎች በጥናትና በእቅድ ተደግፈው በጥድፊያ መሰራት ያለባቸው ስራዎች እንደሆኑ በማስታወስ አልፌያቸዋለሁ፡፡ ሁላችንም ለእዚህ ስራ የሚጠቅሙ ሃሳቦቻችንን አቅማችን በፈቀደ መጠን ማበርከት ይገባናል እላለሁ፡፡

የቅንጅት የተወሰኑ አመራሮች በድርጅቱ ውስጥ ለፈጠሩት ቀውስ በፍጥነት እልባት ሰጥቶ የቅንጅት አመራር ፊቱን በሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለማስፈን ወደተጀመረው ትግል ሁላችንም ፊታችንን እንድናዞር ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በሃገር ውስጥ ከሚደረገው ወሳኝ ትግል በተጨማሪ የቅንጅት አመራር በእስር በነበረበት ወቅት የተገነባውን አለም አቀፍ የድጋፍ የድርጅቶች መዋቅር፣ የተመሰረተውን የዲፕሎማሲና የሚድያ ግንኙነት የበለጠ የሚጠናከርበትን እቅድ በፍጥነት አዘጋጅቶ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ነው፡፡ የውጭው እንቅስቃሴ የቅንጅትን የፖለቲካ አመራር እየጠበቀ እንደሆነ በመረዳት ይህንን አመራር በፍጥነት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የአመራር እጦት፣ ትግሉ በኢትዮጵያ ዴሞክራሰያዊ ስርአት የመገንባት ሳይሆን አመራሩን ከእስር ቤት ማስፈታት ብቻ እንደነበር አድርጎ የሚያየውን የቅንጅት ደጋፊ ቁጥር እያበራከተው ነው፡፡ ይህ ስህተት እንደሆነ፣ መጪው ትግል የበለጠ መደራጀትን፣ የበለጠ መሰባሰብን፣ ገንዘብን፣ እውቀትንና ጉልበትን የሚጠይቅ መሆኑን በማሳየት፣ ይህ የውጭ እንቅስቃሴ በመጠን ይሁን በጥራት አሁን ካለበት ደረጃ የበለጠ እንዲያድግ ፈጣን እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

በጥቅሉ መሰራት ያለባቸውና መሰራት የሚችሉ የቅንጅት ስራዎች በጣም በርካታ ናቸው። የቅንጅት አመራር ባለበት አጠቃላይ በወከባ የተሞላ ሁኔታና ባለው የሰው ሃይል ሁሉንም ስራዎች ሊሰራ አይችልም። የአመራርም ሃላፊነትና ጥበብ ይህ አይደለም። ስራ ለመስራት አቅሙ ብቃቱ ያለቸውን በሽዎች የሚቆጠሩ ደጋፊዎቹንና አባላቱን በሚገባ በማደራጀት መሰራት የሚገባቸውን ስራዎች በማከፋፈል ስራ እንዲሰሩ በማድረግ ይህንን ችግር ቅንጅት በቀላሉ ሊወጣው ይችላል።

በቅንጅት አመራር ላይ የተጫነው የስራ ሸክም ብቻ ሳይሆን ትግሉ ከአመራሩ የሚጠብቀውን መስዋእትነት ሁላችንም የምናየው ነው። በተለይ አንዳንዶቻችን ከውጭ ሆነን ሃሳባችንን በምንሰነዝርበት ወቅት ሃሳባችንን ተቀባይነት ከገኘ፣ ይህንን ሃሳብ ተግባራዊ የሚያደርገው በሃገር ቤት የሚገኘው የቅንጅት አመራር እንደሆነ እናውቃለን። በበኩሌ በእዚህ ጽሁፍ ውስጥ የሰፈሩትን ሃሳቦች ሳቀርብ የቅንጅትን ስራ በሃገር ቤት እንደሚሰሩት የድርጅቱ መሪዎች በእኔ ላይ የሚደርስ የህይወትና የአካል አደጋ አለመኖሩን ሳስብ በውስጤ ትልቅ የሞራል ጥያቄ ይቀሰቅስብኛል። ወያኔ መፈጸም የሚችለውን የመግደል፣ የማሰር፣ የማዋከብ፣ የመሰለልና የማስፈራረት ተግባሩን ከጥቂት አመታት በፊት በቦታው በመገኘት የተገነዘብኩት በመሆኑ፣ ዛሬ በማልገደልበት፣ በማልታሰርብት ሁኔታ በርቀት ተቀምጬ፣ ሞትና እስራትን ሌሎችንም ጥቃቶች ሊያስከትሉ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ አቋም ይዤ መከራከሩ ለህሊናዬ ፈተና ነው። ባለፉት ጥቂት ገጾች የሰነዘረኳቸውን አስተያየቶች ሳሰፍር ህሊናዬን ከሚያመሰቃቅሉ ስሜቶች ጋር እየታጋልኩ እንደሆነ አንባቢ እንዲረዳልኝ እጠይቃለሁ።

በግሌ ሳስበው፣ ዝም ማለቱ ሃሳብ ከማቅረቡ የበለጠ ወንጀል በመሆኑ አማራጭ መስሎ አልታየኝም። አውጥቼ አውርጄ የመሰለኝ በቀና መንፈስ አቅርቢያለሁ። ከእዚህ ሌላ የተለየ አማራጭ አለ የሚሉ ካሉ ሃሰባቸውን ለመስማት በበኩሌ ዝግጁ ነኝ። ሁላችንም ሁኔታው በፈቀደልን መጠን ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ትግል እስከደገፍን የወያንኔ አምባገነናዊ ስርአት እድሜ ማጠሩ የግድ ነው። በመሆኑም እያንዳንዳችን ተመጣጣኝ አስተዋጽኦና መስዋአትነት ባለመክፈላችን መሸበር የለብንም። "ሰው ያለውን ከሰጠ ንፉግ አይባልም" ብለዋልና አበው፣ ከልባችን አቅማችንና ሁኔታችን የሚፈቅድልንን እስካደረግን በቂ ነው።

***በሃገራችን ነጻና ህገ-መንግስታዊ ተቋማት እንዲመሰረቱ ቅንጅት የጀመረው ትግል እንዲሳካ ሁላችንም በያለንበት የአቅማችንን እናበርክት!!***

ጥር፣ 2000 ኢ.ም
አንዳርጋቸው ጽጌ